# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 056 ጥቅምት 26 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# “በአደጋዎች ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች የአካል ድጋፍ የሚያቀርብ ተቋም ተገንብቷል”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- በተለያዩ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች የተሻለ ሰው ሠራሽ የአካል ድጋፍ የሚያቀርብ ተቋም መገንባቱን የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናገሩ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አዲስ የተቋቋመውን የኢትዮጵያ አካል ድጋፍ አገልግሎት ማዕከልን ትናንት መርቀው ከፍተዋል።

በወቅቱ በኢትዮጵያ እንዲሁም በአፍሪካ በሰው ሠራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት በርካታ አካላቸው የጎደለ ዜጎች መኖራቸውን ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ብዙውን ጊዜ በቂ ትኩረት ስለማያገኙ ማገልገል እየቻሉ ተረጂና ተመጽዋቾች የሚሆኑ ዜጎች መኖራቸውን ገልጸዋል።

“በአደጋዎች ጉዳት ለደረሰባቸው... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ሀገራዊ ምክክሩና ፖለቲካ ፓርቲዎች

ዮርዳኖስ ፍቅሩ

ሀገራችን ካላት ረጅም ዕድሜ አንጻር ጥቂቷን 100 ዓመት ብቻ ወደኋላ ዘወር ብለን ብንመለከት ፖለቲካችን መገፋፋትና መጠፋፋት የሰለጠነበት ነው፡፡ በእያንዳንዱ ፖለቲካዊ ሽግግር ብዙዎች ሕይወታቸውን፣ አካላቸውን፣ ንብረታቸውን አጥተዋል፡፡

ጥያቄዎችን ሠላማዊ በሆነ መንገድ ከማንሳት፤ በጠረጴዛ ዙሪያ ከመፍታት፤ በሰከነ መንገድ ለችግሮቻችን መፍትሔን ከመፈለግ ይልቅ ጎራ ለይተን ጦር እየተማዘዝን፤ ሰብዓዊና ቁሳዊ ዋጋ እየከፈልን አለን፡፡ ኢኮኖሚያችንንም እያዳከመው ይገኛል፡፡

የመጣንበትን መንገድ ለልጆቻችን ላለማውረስ፤ ለዘመናት አንድ ቦታ ደጋግመን እንድንረግጥ ካደረገን የጦርነት አዙሪትና የቁርሾ

ሀገራዊ ምክክሩና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ድሬዳዋ ሦስት ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር ላስመዘገቡ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሰጠች

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ሩብ ዓመት ሦስት ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር ካፒታል ላስመዘገቡ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠቱን የድሬዳዋ ከተማ ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ አስታወቀ፡፡


የቢሮው ምክትል ኃላፊና የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኤጀንሲ ኃላፊ አብዲ ሙክታር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ድሬዳዋን የኢንዱስትሪና

ድሬዳዋ .. ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## ፋብሪካው የድንጋይ ከሰልን በመጤ አረም በመተካት በሙከራ ደረጃ ሲሚንቶ ማምረት ጀመረ

ገጽ 4















ወይዘሮ ሊዲያ ግርማ

# ጫኝና አውራጆች ይፈጽሙት የነበረውን ችግር ለመፍታት አዲስ አደረጃጀት ተግባራዊ ሆነ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ጫኝና አውራጆች ኅብረተሰቡ ላይ ይፈጽሙት የነበረውን እንግልትና ችግር ለመፍታት አዲስ አደረጃጀት ተግባራዊ መደረጉን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሠላምና ፀጥታ ቢሮ አስታወቀ።

የቢሮው ኃላፊ ሊዲያ ግርማ እንደተናገሩት፤ ጫኝና አውራጆች ለሕዝቡ ምሬት ምንጭ በመሆን በተለያዩ ሕገ-ወጥ ተግባራት በመፈፀም ዜጎችን ሲያውኩ በመቆየታቸው በአዲስ መልክ ማኅበራት እንዲደራጁ ተደርጓል።

በመዲናዋ የሚገኙ ጫኝና አውራጅ ከማኅበረሰቡ አቅም በላይ ክፍያ በመጠየቅና የኅብረተሰቡ የፀጥታ ስጋት በመሆን ምሬት መፍጠራቸውን ጠቁመው፤ ጫኝና አውራጆችን መልሶ የማደራጀት ሥራው ከአራት ወራት በፊት ለአዲስ አበባ ከተማ የሠላምና ፀጥታ ቢሮ ተሰጥቶት ሲሠራ መቆየቱን አስታውሰዋል።

በአደረጃጀቱ መሠረት አራት ሺህ 829 አባላትን የያዙ 399 ጫኝና አውራጅ ማኅበራት በአዲስ መልክ መቋቋማቸውን አስታውቀዋል።

ማኅበራቱ በአግባቡ ሥራቸውን እያከናወኑ ለፀጥታ ኃይሎች ስጋት ሳይሆን አጋዥ የሚሆኑበትን ሁኔታ መፈጠሩን አመላክተዋል።

ማኅበራቱ ሕግና መመሪያን ተከትለው እንዲሠሩ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሠላምና ፀጥታ ቢሮ በኩል አዲስ መተዳደሪያ ደንብ ተዘጋጅቶላቸው በፍትህ ሚኒስቴር አማካኝነት መጽደቁንም አስታውቀዋል።

በደንቡ ላይም የጫኝና አውራጅ ማኅበራት ሥልጣንና ኃላፊነት የተገለጸ ሲሆን፤ ለእያንዳንዱ ለሚወርድና ለሚጫን ዕቃ ዓይነት ተመን ወጥቶለታል ሲሉ አስረድተዋል።

አዲስ በተዘጋጀው ደንቡ ዙሪያ ለጫኝና አውራጅ ማኅበራቱ አባላት በቂ ሥልጠናዎች እንደሚሰጥ ተናግረዋል።

ማኅበራቱ ከዚህ ቀደም ስምሪት ይሰጣቸው የነበረው በሥራ ዕድል ፈጠራ ኢንተርፕራይዝ ቢሮ እንደነበር አስታውሰው፤ አሁን ላይ የሠላምና ፀጥታ ቢሮ ማኅበራቱን ከማደራጀት ጀምሮ አጠቃላይ አካሄዳቸውን በመገምገም ስምሪት የሚሰጥበት አሠራር መፈጠሩን የቢሮው ኃላፊዋ አንስተዋል።

ማኅበራቱ የሥራ ዕድል ፈጥረው አገልግሎት ከመስጠት ባለፈ በተቀመጠላቸው የዋጋ ተመን መሠረት እንዲሠሩ ጥረት እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።

በአሁኑ ወቅት በአፈጻጸም ላይ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች እንዳሉ ጠቁመው፤ ማኅበረሰቡን አጋዥ የሚሆን አደረጃጀት እንጂ በማኅበረሰቡ ላይ ምሬት ሊፈጥር የሚችል አደረጃጀት እንዳይኖር ቢሮው ያላሰለሰ ጥረት እያደረገ እንደሚገኝ ኃላፊዋ አንስተዋል።

የቢሮው ምክትል ኃላፊ አቶ ሚዴቅሳ ከበደ በበኩላቸው ለኢፕድ እንደጠቆሙት፤ አዲሱ የማኅበራት አደረጃጀት፤ የማኅበራቱን የአገልግሎቱ አሰጣጥ ጥራት ከፍ በማድረግ የሕዝቡን እንግልት ለመቅረፍ የሚረዳ ነው።

እስካሁን 399 ጫኝና አውራጅ ማኅበራት መደራጀታቸውን ጠቁመው፤ ሥራው ባለመጠናቀቁ በቀጣይ የሚደራጁ ማኅበራት መኖራቸውንና ቁጥራቸው ከፍ እንደሚል አስረድተዋል።

ማኅበራቱ በሚደራጁበት ወቅት መነሻ ካፒታል የማይጠየቁ ሲሆን፤ ለተወሰኑ ዓመታት በመሥራት የራሳቸውን ጥሪት ይዘው ወደሌሎች የኢንዱስትሪ ዘርፎች እንዲሸጋገሩ ውጥን መያዙን አመላክተዋል።

# በማዕከላዊ ኢትዮጵያ የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት 50 የሰንበት ገበያዎች አገልግሎት እየሰጡ ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

ሆሳዕና፡- የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት 50 የሰንበት ገበያዎች አገልግሎት እየሰጡ እንደሚገኙ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ አስታወቀ።

የክልሉ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳንኤል ዳምጠው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ክልሉ የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት የሚረዱ 50 የሰንበት ገበያዎች በተለያዩ ከተሞች ተቋቁመው ለአገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ።

በተያዘው በጀት ዓመት ከ70 በላይ የሰንበት ገበያዎች ለማቋቋም ታቅዶ እንደነበር ያስታወሱት አቶ ዳንኤል፤ 50ዎቹ አገልግሎት እየሰጡ በመሆኑ 20 የሰንበት ገበያዎች በቀጣይ ተቋቁመው ለኅብረተሰቡ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋሉ ብለዋል።

የሰንበት ገበያዎች የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት ክልሉ ትኩረት ከሰጣቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው ያሉት አቶ ዳንኤል፤ የሰንበት ገበያዎቹ በሚፈለግባቸው ልክ ሙሉ አገልግሎት እንዲሰጡ ቁጥጥር ይደረጋል ሲሉ ተናግረዋል።

የሰንበት ገበያዎቹን የማጠናከርና ቀሪዎቹን ወደ ሥራ ለማስገባት ከክልል ጀምሮ እስከ ታችኛው የወረዳ መዋቅር ድረስ እየተሠራ መሆኑን አቶ ዳንኤል ጠቁመዋል።

በአምራቹና በሸማቹ መካከል ላይ የሚያጋጥሙ ሕገ-ወጥ ደላሎች ለማስቀረት የሰንበት ገበያው አማራጭ መፍትሔ መሆኑን ተናግረው፤ ሸማቾች በአቅራቢያዎቻቸው በሚገኙ የሰንበት ገበያዎች በመሄድ በርካታ ግብይቶችን እየፈጸሙ መሆኑን አስረድተዋል።

የቢሮ ኃላፊው እንደገለጹት፤ በክልሉ ገበያውን ለማረጋጋት ከሰንበት ገበያ በተጨማሪ አምራቹንና ሸማቹ



አቶ ዳንኤል ዳምጠው

በቀጥታ የማገናኘት እንዲሁም በአቅራቢያ የማይገኙ ምርቶች በሸማች ማኅበራት አማካይነት የማቅረብ ሥራዎች ላይ ትኩረት ተደርጓል።

መሠረታዊ ፍጆታዎች በተለይ የስኳርና የዘይት ምርቶች የአቅርቦት ችግር እንዳይከሰት ከሚመለከተው የፌዴራል መሥሪያ ቤት ጋር በመነጋገር እንዲገባ እየተደረገ ነው ብለዋል።

ለሸማች ማኅበራት ብድር ለማመቻቸት ታቅዶ ወደ ተግባር ተገብቷል ያሉት አቶ ዳንኤል፤ ከመቶ ሚሊዮን ብር በላይ ብድር በማቅረብ እየተሠራ ይገኛል ሲሉ አስታውቀዋል።

በተለይ ለሸማች ማኅበራት የሚፈቀደው ብድር የአቅርቦት ችግር ከመቅረፍ ብሎም ገበያውን ከማረጋጋት ጎን ለጎን ለሥራ ዕድል ፈጠራ አወንታዊ ሚና እንደሚኖረው አቶ ዳንኤል አመላክተዋል።

እንደ ቢሮ ኃላፊው ገለጻ፤ በገበያው ላይ የተለያዩ አሻጥር የሚሠሩና በሕገ-ወጥ መንገድ የሚዛን ቅሸባዎች የሚፈጽሙ አካላት ላይ ቁጥጥር እየተደረገ ይገኛል። በቀጣይም የንግድ ቤቶችን እስከማሸግና የንግድ ፈቃድ እስከ መሰረዝ የሚደርስ ርምጃ ይወሰዳል።

# በክልሉ የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሻሻል ከ94 ሚሊዮን ብር በላይ ከማኅበረሰቡ ተሰብስቧል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሻሻል በማኅበረሰብ ተሳትፎ ከ94 ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰቡን የክልሉ ትምህርት ቢሮ አስታወቀ።

የቢሮው ኃላፊ አወቀ አይሸሽም (ዶ/ር) ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ከሕዝብ በተሰበሰበው ገንዘብ 13 የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችንና ሁለት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ግንባታ ተከናውኗል።

በተጨማሪ 176 የአንደኛ ደረጃ፣ አምስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እድሳት እንዲሁም በ11 የአንደኛ ደረጃና በስድስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመጸዳጃ ቤቶች ግንባታ መከናወኑን ጨምረው አስረድተዋል።

በክልሉ 700 ትምህርት ቤቶች ቢኖሩም ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑት ከደረጃ በታች መሆናቸውን ጠቁመው፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ በተጀመረው የትምህርት ንቅናቄ መሠረት የክልሉን ትምህርት ቤቶች ደረጃ ለማሻሻል ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

የትምህርት ቤት ደረጃ ለማሻሻል በርካታ ግብዓቶች የሚያስፈልጉ በመሆኑ ከማኅበረሰብ ተሳትፎ ተጨማሪ ገንዘብ እየተሰበሰበ መሆኑን ተናግረዋል።

የትምህርት ቤቶችን ደረጃን ለማሻሻል ገቢ ማሳደግ ወሳኝ በመሆኑ ከማኅበረሰብ ተሳትፎ ገንዘብ ከመሰብሰብ በተጨማሪ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች የሚገኝ ከ266 ሄክታር በላይ መሬትን በመጠቀም የተለያዩ የሰብል ዓይነቶች ማልማት መቻሉን አመላክተዋል።

በ2016 የትምህርት ዘመን ከዞን እስከ ትምህርት ቤት በተደረገው የትምህርት ንቅናቄ በ628 ትምህርት ቤቶች



አወቀ አይሸሽም (ዶ/ር)

የመማር ማስተማር ሂደቱ እየተከናወነ ሲሆን፤ ከአንደኛ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ 255 ሺህ 611 ተማሪዎች በትምህርት ገበታቸው ላይ መሆናቸው አብራርተዋል።

በመተከል ዞን በማንዱራ፣ በዳንጉር፣ በጉባ፣ በድባት ወረዳና በተወሰኑ አካባቢዎች በተለያዩ ችግሮች ምክንያት የመማር ማስተማር ሂደት አለመጀመሩን ገልጸው፤ በቅርቡ የመማር ማስተማሩን ለማስጀመር ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል።

ክልሉ ለተከታታይ ሦስት ዓመታት የጸጥታ ችግር አጋጥሞት እንደነበር አስታውሰው፤ አሁን ላይ የተገኘውን አንጻራዊ ሠላም በመጠቀም ከመማር ማስተማሩ ጎን ለጎን ጉዳት የደረሰባቸውን ትምህርት ቤቶች ለመጠገን እየተሠራ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

በክልሉ ከፍተኛ የሆነ የመምህራን እጥረት አለ ያሉት ኃላፊው፤ ችግሩን ለመፍታት በሁሉም ትምህርት ቤቶች መምህራንን የመቅጠርና በግልገል በለስ የመምህራን ኮሌጅ መምህራንን የማሰልጠን ሥራ እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጀመረውን የትምህርት ቤቶች የጥራት ደረጃ የማሻሻል ሥራ ለማከናወን ከመንግሥት አካላት በተጨማሪ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።

# ክልሉ ለኢንቨስትመንት የሚውል 58 ሺህ ሄክታር መሬት አዘጋጅቷል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት ለኢንቨስትመንት የሚሆን 58 ሺህ ሄክታር መሬት ማዘጋጀቱን የኦሮሚያ ክልል ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ቢሮ አስታወቀ። በዘርፉ ለ500 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዷል።

የቢሮው ኃላፊ አሕመድ እንድሪስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2016 በጀት ዓመት በክልሉ የሚገኙ የኢንቨስትመንት አማራጮችን ወደሥራ ለማስገባት እየተሠራ ነው።

በተያዘው በጀት ዓመት ባለሀብቶች በተለያዩ ዘርፎች ተሰማርተው የሚያለሙበት 58 ሺህ ሄክታር መሬት በተለያዩ አካባቢዎች ላይ መዘጋጀቱን አስታውቀዋል።

የተዘጋጀው የኢንቨስትመንት መሬት በማኑፋክቸሪንግ፣ በማዕድንና በሌሎች ዘርፎች ለሚሰማሩ ባለሀብቶች እንደሚተላለፍ ገልጸዋል።

በ2016 በጀት ዓመት የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶችን፣ አርሶ አደሮችን፣ ዩኒየኖችን፣ ወጣት ሥራ ፈጣሪዎችን በአጠቃላይ 30 ሺህ አዳዲስ ኢንቨስተሮችን ለመቀበል ታቅዶ እየተሠራ እንደሚገኝ አመላክተዋል።

በተያዘው በጀት ዓመት ሦስት ወራት ውስጥ ሰባት ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ ሁለት ሺህ 700 አልሚዎች የኢንቨስትመንት ጥያቄ ማቅረባቸውን አመላክተዋል።

የቀረቡት የኢንቨስትመንት ጥያቄዎች በማኑፋክቸሪንግ፣ በግብርና፣ በአገልግሎትና በሌሎች ዘርፎች ላይ መሆኑን አስረድተዋል።

ባለፉት ጊዜያት 400 ባለሀብቶች በአገልግሎት ዘርፍ እንዲሁም 206 ባለሀብቶች በግብርና ዘርፍ እንዲሰማሩ መደረጉን ገልጸዋል።

በሥራ ላይ የሚገኙ ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም ወደ 66 ነጥብ አምስት ለማሳደግ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ አሕመድ፤ ከውጭ ሀገር የሚገቡ የተለያዩ ምርቶች በሀገር ውስጥ በስፋት እንዲያመርቱ ትኩረት ይደረጋል ብለዋል።




**አሕመድ እንድሪስ**

ወደውጭ ሀገር ከሚላኩ የኢንዱስትሪ ምርቶች 800 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት የታቀደ ሲሆን፤ የምርቶችን ጥራት በመጨመር ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

በኢንቨስትመንት ዘርፉ በአጠቃላይ ለ500 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር መታቀዱን ገልጸው፤ የተያዘውን ዕቅድ ስኬታማ ለማድረግ ለባለሀብቶች የተለያዩ ግብዓቶችን ማቅረብ ከሚችሉ የፋይናንስ ተቋማትና ከመንግሥት አካላት ጋር ውይይት ተደርጎ ወደሥራ መገባቱን ጠቁመዋል።

እንደ አቶ አሕመድ ገለጻ፤ በሥራ ላይ የሚገኙ ኢንቨስተሮችን የመደገፍና የመከታተል ሥራ እየተሠራ ሲሆን፤ ያለባቸውን የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የውሃ፣ የመሠረተ ልማት፣ የፋይናንስና የግብዓት ችግሮች በመለየት መፍትሔ እየተሰጠ ይገኛል።

በሥራ ላይ ከሚገኙት ኢንቨስተሮች መካከል 556ቱ ብድር፣ 16ዎቹ መብራት እንዲሁም 136 የሚደርሱት ደግሞ የተለያዩ ማሽኖችን እንደሚፈልጉ በመለየቱ ጥያቄያቸው መልስ እንዲያገኝ ለሚመለከታቸው አካላት ጥያቄ መቅረቡን አስታውቀዋል።

በተጨማሪ በተለያዩ ምክንያቶች ሥራ ያቆሙ 168 ኢንዱስትሪዎች ችግራቸውን በመለየትና ድጋፍ በማድረግ ወደሥራ እንዲመለሱ መደረጉን ገልጸዋል።

# የሌማት ትሩፋት ዘጠኝ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ሊትር ወተት ለማግኘት የተያዘውን ዕቅድ ማሳካት ያስችላል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- የሌማት ትሩፋት በበጀት ዓመቱ የተያዘውን የዘጠኝ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ሊትር ወተት ዕቅድ ለማሳካት እንደሚያስችል ግብርና ሚኒስቴር ገለጸ።

በሚኒስቴሩ የእንስሳትና ዓሣ መሪ ሥራ አስፈጻሚና የወተት ሀብት ልማት ዴስክ ኃላፊ አቶ ለማ ገመዳ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2015/16 የምርት ዘመን ዘጠኝ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ሊትር ወተት ለማምረት ታቅዷል።

በባለፈው የምርት ዘመን ከስምንት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ሊትር በላይ ወተት የተመረተ ሲሆን፤ በተያዘው የምርት ዘመን ዘጠኝ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ሊትር ወተት ለማምረት በትኩረት እየተሠራ ይገኛል።

እንደ ሀገር የተጀመረው የሌማት ትሩፋት መርሃ-ግብር ለወተት ምርት መጨመር ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት አቶ ለማ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በእንስሳት ብዛት ከአፍሪካ ቀዳሚ ብትሆንም የሚፈለገውን መጠን ያህል ወተት ማግኘት አለመቻሉን ጠቁመው፤ ከሕዝቡ ፍላጎት ጋር የሚመጣጠን የወተት ምርት ለማግኘት የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ማዕከላትን በማጠናከርና የመኖ አቅርቦትን ማሻሻል ላይ ትኩረት መደረጉን አመላክተዋል።

የእንስሳት መኖ ሲዘጋጅ የተሻለ ምርት ለማግኘት የሚረዱ ንጥረ ነገሮችን ማካተት እንደሚያስፈልግ ጠቁመው፤ አርሶ አደሩ ጥሩ ዝርያ ያላቸውን ላሞች በስፋት በማርባት ተጨማሪ የወተት ምርት ለማግኘት ጥረት ማድረግ እንዳለበት መልዕክት አስተላልፈዋል።

የእንስሳቱ አመጋገብ ከእንስሳቱ የሚጠበቀውን ምርት ሊሰጥ በሚያስችል መልኩ መሆን እንደሚገባው



ገልጸው፤ የእንስሳት ዝርያ መረጣና የመኖ አቅርቦት ለዘርፉ ውጤታማነት ቁልፍ ጉዳዮች መሆናቸውን አስረድተዋል።

ከዝርያ ማሻሻያ በተጨማሪ የመኖ ማከማቻና ጥራቱን የጠበቀ የእንስሳት ማደሪያ ቦታዎች ዝግጅት ላይ አርሶ አደሩ ትኩረት ሊያደርግ እንደሚገባ አስረድተዋል።

ኢትዮጵያ ከዘርፉ ተጠቃሚ እንድትሆንና ሥራው ውጤታማ እንዲሆን ከክልሎች ጋር በመተባበር እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

የእንስሳትን ምርታማነት ለማሳደግ የዝርያ ማሻሻል፣ የመኖ አቅርቦትና የእንስሳት ማረፊያ ምቹነት ተቀናጅተው መተግበር እንዳለባቸው አስገንዝበው፤ በተናጠል ግለሰቦች ብቻ የሚያካሂዱት ሥራ እንደሀገር ውጤት ስለማያመጣ የኅብረት ሥራ ማኅበራትና ባለሀብቶችም በዘርፉ ሰፊ እንቅስቃሴ ሊያደርጉ እንደሚገባ አመላክተዋል።

እንደ ኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት መረጃ የኢትዮጵያ አጠቃላይ ዓመታዊ የወተት ምርት ከሰባት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ሊትር የማይበልጥ ሲሆን፤ የነፍስ ወከፍ ፍጆታም 66 ሊትር ነው።

ጥራቱንና ደህንነቱን የጠበቀ የወተት ምርት መጠን ጭማሪ ቢያሳይም አንድ ጤነኛ ሰው በዓመት ከሚያስፈልገው 200 ሊትር አንጻር ሲታይ አሁንም ኢትዮጵያ በዘርፉ አነስተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች።

# በኦሮሚያ 265 የተፈጥሮ ማዳበሪያ ማዕከላት እየተገነቡ ነው

**ማርቆስ በላይ**

አምቦ፡- ለአፈር ለምነት መሻሻል ጠቃሚ የሆነ «ቨርሚካልቸር» የተሰኙ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ማምረቻ ማዕከላት በ265 ወረዳዎች እየተገነቡ መሆኑን የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ።

የኦሮሚያ ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ኤሊያስ ከድር እንደገለጹት፤ በሳይንሳዊ አጠራሩ ቨርሚካልቸር የሚባለውን የአፈር ለምነትን ለማሻሻል ጠቃሚ ከሆነ ትል የሚገኘውን የተፈጥሮ ማዳበሪያ በክልሉ ለማምረት ሰፊ ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

በክልሉ በሚገኙ 265 ወረዳዎች ላይ ለሚገነቡት የተፈጥሮ ማዳበሪያ ማምረቻ ማዕከላት 934 ሚሊዮን ብር በጀት መመደቡን አመላክተዋል።

የመሬት የመጎዳትና ምርታማነት መቀነስ አንገብጋቢና ጊዜ የማይሰጠው መሆኑን የገለጹት አቶ ኤሊያስ ላለፉት አምስት ዓመታት የቨርሚኮምፖስት ቴክኖሎጂ ላይ ሰፊ ሥራ ሲሠራ ቆይቷል ብለዋል።

እንደ ክልል ቴክኖሎጂው በአራት ወረዳዎች የተጀመረ መሆኑን ጠቁመው፤ በአሁኑ ወቅት በ254 ወረዳዎች በሚገኙ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ አራት ቀበሌዎችን ማዳረስ መቻሉን አመላክተዋል።

ቴክኖሎጂውን በክልሉ ከሚገኙ ቀበሌዎች ከ50 በመቶ በላይ ላይ ለሆኑት ማዳረስ ተችሏል ያሉት አቶ ኤሊያስ፤ የክልል ችግኝ ጣቢያዎች፣ የአርሶአደሩ ግብርና ማሰልጠኛ ጣቢያዎችና ባለሙያዎች በቴክኖሎጂው ላይ መጠነ ሰፊ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ እያከናነወኑ መሆኑን ገልጸዋል።

ቴክኖሎጂው ከመደበኛ ኮምፖስት በስድስት ዕጥፍ የማልማት አቅም እንዳለው ተናግረው፤ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ረገድ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን አስረድተዋል።

በሌላ በኩል በክልሉ ያለውን መጠነ ሰፊ የእንስሳት ሀብት በመጠቀም የባዮ ጋዝ አቅርቦት ለማዳረስ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ኤሊያስ፤ ቴክኖሎጂው ለኤሌክትሪክ ኃይልና ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል በመሆኑ ትልቅ ለውጥ እያመጣ ነው ብለዋል።

ቴክኖሎጂው ለኃይል ፍጆታነት የሚውል የደን ምንጣሮን በማስቀረት የደን ሽፋንን ለማሳደግ እንደሚረዳ ጠቅሰው፤ ውጤታማነቱን ለማሳደግ ጥረት እንደሚደረግ ተናግረዋል።

እንደ አቶ ኤሊያስ ገለጻ፤ የክልሉ የግብርና ማነቆዎችን ለመፍታት 28 የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢኒሼቲቮች ተቀርጸው እየተሠራባቸው ይገኛል።

ኢኒሼቲቮቹ አበረታችና መጠነ ሰፊ ለውጥ በማምጣት አርሶአደሮችን በሁሉም መስክ ተጠቃሚ በማድረግ ላይ መሆናቸውን አስረድተው፤ በተለይም በፍራፍሬ፣ በበጋ መስኖ ስንዴ፣ በሩዝና የተለያዩ ሰብል ልማት ሥራዎች ውጤት እየተመዘገበ መሆኑን አስገንዝበዋል።

# ፋብሪካው የድንጋይ ከሰልን በመጤ አረም በመተካት በሙከራ ደረጃ ሲሚንቶ ማምረት ጀመረ

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡- ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ ለኃይል አቅርቦት የሚጠቀመውን የድንጋይ ከሰል በመጤ አረም (በወያኔ አረም) በመተካት በሙከራ ደረጃ ሲሚንቶ ማምረት መጀመሩን ኢስት አፍሪካ ሆልዲንግ አስታወቀ፡፡

በኢስት አፍሪካ ሆልዲንግ የኢነርጂ ዘርፍ አስተባባሪ አቶ ገዛኸኝ አምዛ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኢስት አፍሪካ ሆልዲንግ ስር የሚተዳደረው ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ ለኃይል አቅርቦት የሚያውለውን የድንጋይ ከሰልን በሳይንሳዊ አጠራሩ በፕሮሶፒስ ጁሊፎራ (በወያኔ አረም) በመተካት ሲሚንቶ ማምረት የሚያስችል የሙከራ ሥራ ጀምሯል።

የወያኔ አረሙ ከአፋርና ሱማሌ ክልሎች እየተወሰደ በድሬዳዋ ናሽናል ሲሚንት ለምርት ግብዓትነት እየዋለ መሆኑን በመግለጽ፤ ከ100 ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ አረሙን ለመንቀልና ለማቃጠል የሚረዳ ማሽን ፋብሪካው ጥቅም ላይ ማዋሉን ገልጸዋል።

በአፋር ክልል ከ300 ሄክታር በላይ መሬት ላይ የሚገኝ የወያኔ አረምን በመጠቀም ሲሚንቶ የማምረት ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ጠቁመው፤ አረሙ በአፋርና በሱማሌ ክልሎች ከሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ ተንሰራፍቶ የሚገኝ በመሆኑ ለሲሚንቶ ፋብሪካዎች የሚሆን ሰፊ ግብዓት ሀገር ውስጥ እንዳለ አመላክተዋል።

በአሁኑ ወቅት የወያኔ አረሙን ከስሩ ነቅሎ ከሚያወጣው ማሽኖች በተጨማሪ ሠራተኞች ተመድበው አስፈላጊውን ግብዓት እያሰባሰቡ መሆኑን ገልጸው፤ በቀጣይ ሰፊ በጀት በመመደብ ተጨማሪ ማሽኖችን ለማስገባት ጥረት እንደሚደረግ ተናግረዋል።

አቶ ገዛኸኝ እንዳስታወቁት፤ የወያኔ አረምን ለታሰበለት ጥቅም በማዋል መሬቱ ለእርሻና ለግጦሽ አገልግሎት እንዲውሉ እየተደረገ ይገኛል።

አረሙን ለፋብሪካው ግብዓትነት በስፋት መጠቀም ከተቻለ የሲሚንቶ ማምረቻ ዋጋ ላይ የራሱ የሆነ በጎ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ያሉት የኢነርጂ ዘርፍ አስተባባሪው፤ በቀጣይ ውጤታማነቱ ሲጠናከር እንደሀገር ያለውን የሲሚንቶ ዋጋ ግሽበትን ለማረጋጋት ይረዳል ብለዋል፡፡

ፕሮጀክቱ የአረንጓዴ ኢነርጂ ትግበራ አካል በመሆኑ ከሲሚንቶ ፋብሪካዎች የሚለቀቀውን የካርበን ዳይኦክሳይድ ልቀትን እንደሚቀንስ የገለጹት አስተባባሪው፤ ለድንጋይ ከሰል የሚውለውን የውጭ ምንዛሬ በማስቀረት ረገድ ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል ሲሉ አመላክተዋል።

የሙከራ ውጤቱን በቅርቡ ለሚመለከተው አካልና ለግሉ ዘርፍ ለማሳወቅ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀው፤ የሙከራው ሥራው እንደተጠናቀቀ ኢንቨስትመንቱን የማስፋፋት ሥራ እንደሚከናወን ገልጸዋል።

በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የአየር ንብረት ለውጥ ዘርፍ የሪፎርም ፐርፎርማንስ ፕሮጀክት የቴክኒክ ሥራዎች አስተባባሪ አቶ ዳዊት አለሙ በበኩላቸው፤ ፕሮጀክቱ በሙከራ ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑ ውጤታማነቱን በቀጣይ በማየት በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል ብለዋል።

ለፕሮጀክቱ ሙከራ ከሁለቱም ክልሎች የሚገኘውን አረም የሚነቅል፣ የሚቆራርጥና የሚፈጭ ማሽን ጥቅም ላይ መዋሉን አስታውቀው፤ እስከአሁን ከአምስት ሺህ ቶን በላይ አረም በመሰብሰብ ለሲሚንቶ ምርት ኃይል አቅርቦት ግብዓትነት መዋሉን ተናግረዋል።

አረሙ ከሀገር ውስጥ የድንጋይ ከሰል የተሻለና ኃይል የሚሰጥና ለድንጋይ ከሰል የሚወጣውን ወጪ የሚያስቀር መሆኑን ገልጸው፤ በቀጣይ የአዋጭነት ሁኔታውን ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማጥናት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

የፕሮጀክቱ ዓላማ ከአምራች ኢንዱስትሪ የሚለቀቀው የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መቀነስና ወጪ ቆጣቢ አሠራርን ማስፋት ነው ያሉት አቶ ዳዊት፤ የሙከራ ሥራው ከአንድ ዓመት በኋላ እንደተጠናቀቀ ውጤታማነቱን ወደ ሌሎች ፋብሪካዎች የማስፋት ሥራ ይሠራል ብለዋል።

# ድሬዳዋ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የንግድ ማዕከል ለማድረግ የሚያስችል ሰፊ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል።

በ2016 በጀት ዓመት ለ60 ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ፤ በሩብ ዓመቱ ሦስት ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር ካፒታል ላስመዘገቡ 28 ባለሀብቶች ፈቃድ መሰጠቱን አመላክተዋል።

ፈቃዱ የተሰጠው ለከፍተኛ፣ መካከለኛና አነስተኛ ኢንቨስትመንት አንቀሳቃሾች መሆኑን ገልጸው፤ በአግሮ ኢንዱስትሪ፣ በምግብና መጠጥ፣ በመኪና መገጣጠሚያ፣ በብረታብረትና ፈርኒቸር ዘርፎች ላይ የሚሳተፉ ባለሀብቶች ቦታ ማግኘታቸውን አስታውቀዋል።

ፈቃድ የወሰዱ ባለሀብቶች በሙሉ አቅማቸው ወደሥራ ሲገቡ አዳዲስ የሥራ ዕድል ለመፍጠር፣ የተለያዩ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ለመተካትና ሌሎች ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎችን እንደሚያስገኙ አስረድተዋል፡፡

በከተማዋ የሚገኙ አምራች ኢንዱስትሪዎች ከውጭ ሀገራት የሚገቡ ምርቶችን በመተካት፣ በሥራ ዕድል ፈጠራና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ውጤት እየተመዘገበ መሆኑን ገልጸው፤ በቀጣይም በተለያዩ ዘርፎች ኢንቨስተሮችን ለመሳብ በትኩረት እንደሚሠራ አብራርተዋል፡፡

እንደ አቶ አብዲ ገለጻ፣ በኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ዘርፉ በበጀት ዓመቱ ሦስት ወራት ከሦስት ሺህ በላይ የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡

በድሬዳዋ ከተማ የተከፈተው ነፃ የንግድ ቀጣናም ለከተማዋ አምራች ኢንዱስትሪዎች መነቃቃትን በመፍጠር ለዜጎች የሥራ ዕድል እየፈጠረ ነው ብለዋል፡፡

ባለሀብቶች ከተማውን የሚያሳድጉና ማኅበረሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ዘርፎች ላይ እንዲሳተፉ በጥናት የመለየት፣ መሠረተ ልማቶችን የማሟላትና የኢንቨስትመንት ቦታን የማመቻቸት ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በከተማው የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ከተጀመረ ጀምሮ በርካታ ውጤቶችን አስገኝቷል ያሉት አቶ አብዲ፤ የኢንቨስትመንት ዘርፉን ከማነቃቃት ባለፈ ተዘግተው ከነበሩ ከ10 በላይ ኢንዱስትሪዎችን ወደሥራ መመለስ እንደተቻለ አስረድተዋል።

አምራች ኢንዱስትሪዎች ከኤሌክትሪክ ኃይል፣ ከግብዓት፣ ከመንገድና ከውሃ መሠረተ-ልማት አቅርቦት ጋር እያጋጠሟቸው የሚገኙ ችግሮችን በመለየት ተገቢ የመፍትሔ ርምጃ እየተወሰደ እንደሚገኝም ገልጸዋል፡፡

ማኅበረሰቡ ሀገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶችን በኩራት ሊጠቀሙ ይገባል ያሉት አቶ አብዲ፤ የሀገር ውስጥ ምርቶች ተፈላጊነት ሲጨምር ከሀገር ውስጥ አልፎ የውጭ ኢንቨስተሮችን መሳብ ይቻላል ብለዋል፡፡

ድሬዳዋን የኢንዱስትሪና የንግድ ማዕከል ለማድረግ ባለሀብቶች ወደከተማዋ መጥተው በተለያዩ ዘርፎች ኢንቨስት እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# “በአደጋዎች ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በለውጡ ወቅት እንደመንግሥት አካል ጉዳተኞችን የሚያስታውስ ሥራ እናከናውን ብለን ስንነሳ ብቁ ባለሙያዎች ቢኖሩም በዘርፉ በቂ ግብዓት የተሟላላቸው ተቋማት እንዳልነበሩ አስረድተዋል።

አሁን ላይ ዘመናዊ መሣሪያዎች ያሉትና ይበልጥ የተማሩ ባለሙያዎች የታከሉበት እንዲሁም አካል ጉዳተኞችን በማገዝ ረገድ ሰፊ ሥራ የሚከናወንበት ተቋም መገንባት እንደተቻለ ጠቁመዋል።

በጦርነትም ሆነ በተለያዩ አደጋዎች እጃቸውን አሊያም እግራቸውን ያጡ ዜጎች በማዕከሉ ገብተው አጋዥ አካል (ሰው ሠራሽ አካል) ተገጥሞላቸው የሚንቀሳቀሱበትና ማገልገል የሚችሉበት ዕድል እንደተፈጠረላቸው ተናግረዋል።

ተቋሙ በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት የአካል ጉዳተኛ ለሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች በሀገር ውስጥ አጋዥ ቁሶችን አምርቶ ለማቅረብ የተቋቋመ ማዕከል ነው ብለዋል።

ማዕከሉ በቀጣይ በተለያዩ አደጋዎች ምክንያት የጆሮ ማዳመጥ ችግር ያለባቸውን የማየት ችግር ያጋጠማቸውን ዜጎች ጭምር ማገዝ የሚችልበትን አቅም እንዲያገኝ በትኩረት ሊሠራ እንደሚገባ አመላክተዋል።

ተቋሙ በቴክኖሎጂ አማካኝነት አይነ-ስውራንን የሚያግዙ መነጽሮችን ወደ መሥራት ማደግ አለበት ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስገንዝበዋል።

ታካሚዎች በተቋሙ ለሕክምና በሚንቀሳቀሱበት ወቅት አዕምሯቸውን የሚያድሱ አረንጓዴ መናፈሻዎች፣ የስፖርት ማዕከላትና ልምምድ የሚሠሩባቸው ንጹህ ስፍራዎች በመገንባታቸው ጥሩ ሥራ ተከናውኗል ሲሉ አወድሰዋል።

የሰው ልጅ ከአካል ስብራቱ ይልቅ ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስደው የአዕምሮ ስብራቱ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ አዕምሯችን ሲጎዳ ነፀብራቁ አካላችን ላይ ስለሚታይ መንፈስን የሚያድሱ መሠረተ ልማቶች በተቋሙ መገንባታቸውን በጥሩ ጎኑ አንስተዋል።

አገልግሎቱን ማሳደግ ከተቻለ ከአፍሪካም ጭምር በዘርፉ አጋዥ የሆነ ሥራ ለማከናወን መነሻ የሚሆን ማዕከል መቋቋሙን አስታውቀዋል። ማዕከሉን እንዲቋቋም የዩናይትድ ዐረብ ኤምሬትና የተለያዩ ሀገራት ላደረጉት ድጋፍም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምስጋና አቅርበዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተቋሙን የተለያዩ ሥራዎች በመጎብኘት የአገልግሎቱን ተጠቃሚዎች አነጋግረዋል።

የኢትዮጵያ አካል ድጋፍ አገልግሎት በቴክኖሎጂ በታገዘ መንገድ ጥራት ያለውና ደንበኛ ተኮር የሰው ሠራሽና የአካል ድጋፍ አገልግሎቶችን ለኅብረተሰቡ እየሰጠ መሆኑን ተገልጿል።

በምርቃቱ ወቅት የጤና ሚኒስቴር ያዘጋጀውን ዕቅውናና ሽልማት የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ለማዕከሉ ግንባታ አስተዋጽኦ ላበረከቱ አካላት አበርክተዋል።

በሥነሥርዓቱ ላይ የመከላከያ ሚኒስትር አብርሃም በላይ(ዶ/ር)፣ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ የጤና ሚኒስትር ሊያ ታደሰ (ዶ/ር) እና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ፖለቲካ መውጣት ይገባናል፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ፣ በችግሮቻችን ላይ በመምከር፣ ልዩነቶቻችንን በጠረጴዛ ዙሪያ መፍታት ስንችል ነው፡፡

እንደ ሀገር መግባባት ባልቻልንባቸው፣ አቋም ይዘን ጎራ በለየንባቸው ጉዳዮች ላይ መምከር እንደሚያሻን በኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ዘንድ ታምኖበት ሀገራዊ ምክክሩን ይመራ ዘንድ የምክክር ኮሚሽን ተቋቁሟል፡፡

ኮሚሽኑ ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ ለብሔራዊ ምክክሩ ስኬት አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ዝግጅቶችን እያገባደደ ይገኛል፡፡ ሠላምን የሚሻው የኢትዮጵያ ሕዝብም ምክክሩ «ሀገራዊ ችግሮቻችንን ይፈታልናል» «ያቀራርበናል» «ያግባባናል» ብሎ ትልቅ ተስፋን ጥሎበታል፡፡ በምክክር ኮሚሽኑ ለሚካሄደው ሀገራዊ ምክክር የፖለቲካ ፓርቲዎች ከባለድርሻዎች መካከል ይገኙበታል፡፡

አቶ ሙባረክ ረሺድ፣ በነፃነትና እኩልነት ፓርቲ አመራርና የፓርቲው ብሔራዊ ምክር ቤት አባል ናቸው። ሀገራችን ካሳለፈችውና ካለችበት ፖለቲካዊ ሁኔታ አኳያ ብሔራዊ ምክክሩ ከአስፈላጊም በላይ ነው ብለው ያምናሉ፡፡

በሀገራችን ለረጅም ጊዜ ቁርሾ የነበሩ እንደ ሀገር ልንስማማባቸው ሲገባ በልዩነት የቆምንባቸው ብዙ ጉዳዮች መኖራቸውን ያነሱት አቶ ሙባረክ፣ ባለፉት ጊዜያት በሀገራችን የሀገራዊ ምክክር ጉዳይ ትኩረት ሳይሰጠው የቆየ ቢሆንም፣ አሁን ግን ሀገራዊ ምክክር የማካሄድ አስፈላጊነት ላይ መንግሥትም አምኖበት በኮሚሽን ደረጃም ራሱን የቻለ ተቋም ተቋቁሞ ምክክሩን ለማካሄድ እየተሄደበት ያለውን ሂደት ፓርቲያቸው በተስፋ እንደሚያየው ገልጸዋል፡፡

ተከተል አጋፋሪ (ዶ/ር)፣ የኢትዮጵያ ሶሻሊስት ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ሲሆኑ፣ ፓርቲያቸው ለሀገራችን መፍትሔ የሚያመጣው ሀገራዊ ምክክር እንደሆነ ከሌሎች ይህን ሃሳብ ከሚጋሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በመሆንና በተናጠልም በተደጋጋሚ ጥያቄ ሲያነሳ እንደቆየ አንስተው፣ ፓርቲያቸው ምክክሩ ለሀገራችን ትልቅ መፍትሔ ያመጣል ብሎ ተስፋ እንደሚያደርግም ተናግረዋል፡፡ ሀገራችን ከገባችበት አለመረጋጋት፣ ጥርጣሬ፣ አለመተማመንና እርስ በእርስ አለመከባበር ሊያወጣት የሚችለው ውይይት ነው የሚል አቋም እንዳለውም ያነሳሉ፡፡

እርሳቸው እንዳሉት፣ ሀገራችን ያለችበት ሁኔታ ተስፋ የሚያስቆርጥ ቢመስልም፣ የሰው ልጅ ከፈጣሪ ዘንድ የመመካከርና ችግሮቹን በራሱ የመፍታት ተፈጥሯዊ ባህርይ የተሰጠው ነውና የኢትዮጵያ ሕዝብም ይህን ተጠቅሞ መፍትሔ ማምጣት ይችላል የሚል አቋም አላቸው፡፡

የፖለቲካ ፍላጎቶች ሕዝቡ መፍትሔ ከሚሻባቸው ጉዳዮች ጋር ፈጽሞ መቀላቀል የለባቸውም በማለት፣ ይህ ካልሆነ ግን፣ ምክክሩ የተፈለገውን መፍትሔ ሊያመጣ እንደማይችል ለዚህም መንግሥትና ተፎካካሪ ፓርቲዎች ሕዝቡን ሊያስቀድሙና ከታችኛው ማኅበረሰብ የሚነሳውን ጥያቄ ወደ መድረክ እንዲያመጡ፤ አጀንዳ ሊሆኑ የሚገባቸው ጉዳዮች ሳይደመጡ እንዳይቀሩ በማድረግ በኩል ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ተከተል(ዶ/ር) ጠይቀዋል፡፡ ምክክሩ በተገቢ መልኩ ከተያዘና አካታችና አሳታፊ ሆኖ ከተመራ ውጤታማ የማይሆንበት ምክንያት እንደሌለም አበክረው ይናገራሉ፡፡

# ሀገራዊ ምክክሩና...



ዶ/ር ተከተል አጋፋሪ



አቶ ሙባረክ ረሺድ



አቶ አዲሱ አረጋ

የምክክሩን አሳታፊነት በተመለከተ አቶ ሙባረክ፣ መላው ኢትዮጵያውያን፣ መንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ሌሎችም አካላት ይህንን ምናልባትም መልሰን ልናገኘው የማንችለውን ዕድል ሊያበላሹ ከሚችሉ ነገሮች መጠበቅና ለጋራ መፍትሔ በንቃት መሳተፍ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

ከምክክር ኮሚሽኑ አባላት አመራረጥ ጋር ተያይዞ ቅሬታዎች ቢኖሩንም እንደ ሀገር ለሀገራዊ ምክክር ሂደት አዲስ መሆናችንን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በሂደት እየተማርንና እየለመድን እንሄዳለን በሚል መርህ የምክክሩን ሂደት ለማገዝና በሂደቱም ለመሳተፍ እንደ ፓርቲ ቁርጠኛ አቋም እንዳላቸው የገለጹት አቶ ሙባረክ፣ በተግባርም እንደ ፓርቲ ሂደቱ ላይ ያሉ እንከኖችን ከመንገር ጀምሮ፣ በሌሎችም ተግባሮች ሂደቱን እያገዙ እንደሚገኙም ጠቁመዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ፣ (ኢሶዴፓም) እንደ አንድ ባለድርሻ አካል ምክክሩን በተስፋ እንደሚጠባበቅ የተናገሩት ተከተል (ዶ/ር)፣ በተግባርም ፓርቲው ኮሚሽኑ በሚጋብዛቸው መድረኮች ሁሉ ከየአደረጃጀቱ ሰዎችን በመወከል እያሳተፈ እንደሚገኝና፤ ለተሳታፊዎችም ሥልጠናዎችንም በመስጠት አቅም እየገነባ እንደሚገኝ ገልጸው፤ በግልም እንደ ፓርቲም ለሀገራዊ ምክክሩ ያላቸውን ዝግጁነት ገልጸዋል፡፡

ሀገራዊ ምክክር የሚካሄደው በተረጋጋ ሁኔታ ውስጥ ነው ያሉት አቶ ሙባረክ፤ በሀገሪቱ ውስጥ ነፍጥ ያነገበ አካል እያለ እንደ ሕዝብ ምክክር አደርጋለሁ ማለት ይከብዳል፤ ችግሮችን በነፍጥ ለመፍታት ከመሞከር ይልቅ ሁለቱም ወገኖች ልዩነታቸውን ወደ ሀገራዊ ምክክሩ ማምጣት መፍታት ይገባቸዋል፡፡ እርሳቸው እንዳሉት፣ ውይይት የሚካሄደው ነፍጥ ያነገቡ ጉዳዮች ላይም ሆደ ሰፊ ሆኖ በመቀራረብ ለመፍታት ነው፡፡

አቶ ሙባረክ እንደተናገሩት፣ በሁሉም ኢትዮጵያዊ ዘንድም የጦርነት አጀንዳን ትቶ ችግሮች የሚፈቱልኝ በጦርነት ሳይሆን በውይይት ነው ብሎ ማመንና፣ ሜዳውንም ለዚህ ዝግጁ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

አቶ ሙባረክ፣ ምክክሩ የሁሉንም ትብብር የሚሻ እንጂ የተቋቋመው ኮሚሽን ብቻውን ሊያሳካው የሚችል እንዳልሆነ አስምረውበታል፤ ኮሚሽኑ ሀገራዊ ምክክሩን አመቻች ሲሆን፣ ስኬታማነቱ ግን በሁሉም ባለድርሻ አካላት እጅ ነው የሚለውንም አክለዋል፡፡

የብልጽግና ፓርቲ ዓለም አቀፍ ግንኙነት ዘርፍ ኃላፊ አቶ አዲሱ አረጋ በአንድ ወቅት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት ሃሣብ፣ እንደ ብልጽግና ፓርቲ በሀገራችን ሀገራዊ ምክክር እንዲደረግ ሙሉ ቁርጠኝነት እንዳለው በማንሳት፣ ኮሚሽኑን ከሚመሩ ሰዎች ጥቆማ ጀምሮ ኮሚሽኑን በማዋቀር እና በማደራጀት ሕዝብን አሳታፊ ባደረገና ተጠሪነቱም ለሕዝብ ተወካዮች ሆኖ እንዲቋቋም የተሄደበት ሂደት ለዚህ ማሳያ ነው ብለዋል፡፡

በቀጣይም እንደ ገዢ ፓርቲ በምክክር ሂደቱ የሚጠበቅበትን ሁሉ ለማድረግ ትልቅ ቁርጠኝነት እንዳለውም ገልጸዋል፡፡ አቶ አዲሱ፣ በምክክር ሂደቱ የሀገራችን ፖለቲካ ከሁከት፣ ከጎዳና ላይ ነውጥና ከጠብመንጃ አፈሙዝ ተላቆ ወደ ጠረጴዛ ዙሪያ እንደሚመጣና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደቱም ወደ ተሻለና ወሳኝ ወደ ሆነ ምዕራፍ እንደሚያሸጋግረው ያላቸውን ጽኑ እምነት ገልጸዋል፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎቹ እና የኢትዮጵያ ሕዝብ ተስፋው እውን ይሆን ዘንድ ከዚህኛውና ከዚያኛው ጫፍ እንድንቆም ባደረጉን ጉዳዮቻችን ላይ ለመምከር እንትጋ፤ ብሔራዊ አንድነታችንን በማጠናከር ልጆቻችን ሠላም ወጥተው የሚገቡባት፤ አዛውንቶች የሚጦሩበት ከጦርነት ተላቃ ሠላም የሰፈነባት ሀገርን ለትውልድ እናውርስ!

# ርዕሰ አንቀፅ

## የመንግሥት የግብርናው ዘርፍ ቁርጠኝነት ሌሎች መገለጫዎች!

የግብርናው ዘርፍ ምርትና ምርታማነት እያደገ መጥቷል፡፡ ሀገሪቱ ግብርናው የኢኮኖሚው መሠረት መሆኑን በመገንዘብ ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥታ መሥራቷን ተከትሎ ነው ይህ ዕድገት ሊመዘገብ የቻለው፡፡ በዘር የሚሸፈነው ማሳ እየጨመረ መምጣት፣ የኩታ ገጠም እርሻና ሜካናይዜሽንና የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት መስፋፋትና የመንግሥት ድጋፍና ክትትል ለምርትና ምርታማነቱ እያደገ መምጣት ከሚጠቀሱ ምክንያቶች መካከል ይገኙበታል፡፡

በዘርፉ እየተመዘገበ ያለው የምርትና ምርታማነት እድገት ሀገሪቱ በዘርፉ ካላት እምቅ አቅምና ፍላጎት አኳያ ሲታይ በቂ ተብሎ የሚወሰድ አይደለም፡፡ እየተተገበረ በሚገኘው የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያም የግብርናው ዘርፍ ከአምስቱ የኢኮኖሚው ምሰሶዎች አንዱ እንደመሆኑ ከዘርፉ ብዙ ይጠበቃል፡፡ በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው የአስር ዓመቱ እቅድ ከግብርናው ዘርፍ ብዙ ይጠበቃል፡፡ የምርትና ምርታማነት መጨመር አንድ ነገር ሆኖ፣ እንደ ቤተሰብም እንደ ሀገርም የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ ለኢንዱስትሪው ልማት የሚሆን አቅም ከግብርናው ማግኘትና ከውጭ የሚገባውን ስንዴ በሀገር ውስጥ መተካት አልፎም ተርፎ ስንዴ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ከግብርናው ዘርፍ የሚጠበቁ ተግባሮች ተደርገው እየተሰራባቸው ናቸው፡፡

እንደሚታወቀው መንግሥት ለግብርናው ዘርፍ ልዩ ትኩረት በመስጠት ምርትና ምርታማነት የበለጠ እንዲያደግ እየሠራ ይገኛል፡፡ መንግሥት ለዘርፉ የሚያደርጋቸውን የተለያዩ ድጋፎች አሁንም አጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ ከድጋፎቹ አንዱ የአፈር ማዳበሪያ ማቅረብ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በ2014/15 የምርት ዘመን ለማዳበሪያ ግዥ 15 ቢሊየን ብር ያወጣው መንግሥት፣ በ2015/16 የምርት ዘመን 21 ቢሊየን ብር አውጥቷል፡፡ ዘንድሮ 23 ሚሊየን ኩንታል ማዳበሪያ እንዲቀርብ እያደረገ ነው፡፡

የፋይናንስ ተቋማት ለግብርናው ዘርፍ ትኩረት እንዲሰጡ ሲወተውት ቆይቷል፡፡ መንግሥት የፋይናንስ ተቋማት ከአርሶ አደሩ ይልቅ በሕንጻ ግንባታ ለተጠመዱ ባለሀብቶች ብድር እየሰጡ ካሉበት ሁኔታ ወጥተው ለገንዘቡ ባለቤት ለአርሶ አደሩ የፋይናንስ አቅርቦት እንዲያደርጉ በተደጋጋሚ አስገንዝቧል፡፡ ይህ የመንግሥት ማሳሰቢያ በፋይናንስ ተቋማቱ ተደምጦ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተቋማቱ አርሶ አደሩን ተደራሽ ማድረግ ጀምረዋል፡፡ ለግብርናው ዘርፍ የሚቀርቡት ፋይናንስ እየጨመረ መምጣቱን መንግሥትም አረጋግጦታል፡፡

መንግሥት ለዘርፉ እድገት ማነቆ የሆኑትን ችግሮች ፈጥኖ መፍታቱን ቀጥሎበታል፡፡ ለእዚህም በቅርቡ በአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት ላይ የወሰደው ርምጃ ይጠቀሳል፡፡ ባለፈው ዓመት በአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት እና ሥርጭት ላይ ክፍተት ታይቶ እንደነበር ይታወሳል፡፡ መንግሥት ይህን ክፍተት ለመድፈን ዘንድሮ በማዳበሪያ ግዥና አቅርቦት ላይ አስቀድሞ መሥራት ጀምሯል፡፡ በእዚህም ለ2016/17 የምርት ዘመን 23 ሚሊየን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ለማቅረብ እየሠራ ይገኛል፡፡ ከዚህ ውስጥም አንድ ሚሊየን 327 ሺ 574 ሜትሪክ ቶን የአፈር ማዳበሪያ ግዥ የተፈጸመ ሲሆን፣ የቀሪው ግዥም በሂደት ላይ ነው፡፡

ዩሪያ የአፈር ማዳበሪያ የጫነችው የመጀመሪያዋ መርከብም በቅርቡ ጅቡቲ ወደብ መድረሷን ተከትሎ በግብርና ሚኒስትሩ የተመራ የልዑካን ቡድንም ማዳበሪያ ለማጓጓዝ እየተደረገ ያለውን ጥረት ሰሞኑን በጅቡቲ ተገኝቶ ተመልክቷል፡፡ ይህም መንግሥት የማዳበሪያ ግዥ በወቅቱ ከመፈጸም በተጓዳኝ የማጓጓዝ ሂደቱ የደረሰበትን ደረጃ እየተከታተለ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትና ክትትል ላይ እየወሰደ ያለው ይህ ሁሉ ርምጃ፣ ለግብርናው ዘርፍ ምርትና ምርታማነት እድገት ያለውን ቁርጠኝነት በተጨባጭ ያረጋገጠበት ሌላ ወሳኝ መንገድ ነው፡፡

መንግሥት ቀደም ሲልም ይህን ቁርጠኝነቱን በሰብል ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ተባዮችን በወቅቱ ለመከላከል እንዲያስችል በኬሚካል መርጫ አውሮፕላኖች አቅርቦት ላይ አሳይቷል፡፡ ከጥቂት ዓመታት በፊት በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች እንደ አንበጣ፣ ግሪሳ ወፍ የመሳሰሉት ጸረ ሰብል ተባዮች በቡቃያና በደረሰ ሰብል ላይ ጉዳት ሲያደርሱ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ረጅም ጊዜ ሲወስድና ትልቅ አጀንዳ ሆኖ ሲያነጋግር እንደነበር ይታወሳል፤ ጸረ ሰብል ተባዮቹን ለመከላከል የኬሚካል መርጫ አውሮፕላኖችን በትብብር ለማግኘት የተለያዩ ሀገሮችን እስከ መጠቀም መደረሱ ይታወቃል፡፡ ለሰብል ተባይ መከላከሉ ሥራ አርሶ አደሩ ብቻ ሳይሆን የከተማ ነዋሪዎችን፣ የመከላከያ ሠራዊትንና የመሳሰሉትን የኅብረተሰብ ክፍሎች በማስተባበር ይሠራ እንደነበር ይታወሳል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በተለያዩ አካባቢዎችና ወቅቶች የተከሰቱ የተምች፣ የአንበጣና የግሪሳ ወፍ መንጋዎችን በቅድሚያ በአርሶ አደር ደረጃ በመከላከል ከዚህ ያለፈውን ደግሞ በአውሮፕላን ኬሚካል በመርጨት መከላከል እየተቻለ ነው፡፡ ጸረ ሰብል ተባዮች በሰብል ላይ ያደርሱ የነበረውን ጉዳት መቀነስ መቻሉ ለምርትና ምርታማነቱ ማደግ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ መንግሥት በእዚህ በኩል ሀገሪቱ አቅም ማጎልበት የቻለችበትን ሁኔታ በፍጥነት መፍጠሩ ለግብርናው ዘርፍ ያለው ቁርጠኝነት ሌላው መገለጫ ነው፡፡

መንግሥት የግብርናውን ዘርፍ ዋና ዋና ማነቆዎች በተለይም አነጋጋሪ ሆነው የቆዩ ችግሮችን ለመፍታት የሄደባቸው ርቀቶችና የተገኙት ተጨባጭ ውጤቶች የቁርጠኝነቱ መገለጫዎች ናቸው፡፡ ችግሮች ዳግም ችግር እንዳይሆኑ ማድረግ መቻልም በራሱ በርግጥም ቁርጠኛ መሆኑን ያመለክታል!

**አዲስ ዘመን**
ኢፕድ
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የባህር በር ጥያቄ የነበረ ያለና ተገቢውን ምላሽ እስኪያገኝ የሚቀጥልም ነው !!!

ሰውመሆን መልካም

ከሰላሳ ዓመት በፊት ኢትዮጵያ ሁለት የራሷ ወደቦች የነበሯት ሀገር ነበረች። በየትኛውም ዘመን የነበሩ የኢትዮጵያ መንግሥታት በወደብ ጉዳይ የሄዱበት ርቀት ቢለያይም ኢትዮጵያ ወደብ አያስፈልጋትም ወይንም የወደብ ታሪኳ ተዘግቷል ብለው አያውቁም። ዛሬም በወደብ ጉዳይ የተነሳው እንወያይበት እንምከርበት የሚለው ሃሳብ የዚሁ እውነታ አንድ አካል ነው።

በወደብ ጉዳይ ከግማሽ ምእተ ዓመት በፊት የነበረውን እንቅስቃሴ ብቻ እንኳን ብንመለከት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በሚያዝያ 25 ቀን 1950 ዓ.ም ከዩጎዝላቪያ መንግሥት በብድር በተገኘ በ26 ሚሊየን አንድ መቶ ሺህ ብር ወጪ «ፖም ግራድ» በተባለ የዩጎዝላቪያ ኩባንያ የአሰብ ወደብ ግንባታን መሠረት አስጥለው ማስጀመራቸው ይታወሳል።

የወደቡ ግንባታም ከአራት ዓመታት በኋላም ተጠናቆ ራሳቸው በተገኙበት ለመመረቅ በቅቷል። ይህ የንጉሱ ተግባር በወቅቱ አንድ ሀገር ከአንድ በላይ ወደብ እንደሚያስፈልጋት ተረድተው እንጂ የምጽዋ ወደብ በእጃቸው እንደነበር ልብ ሊባል ይገባል።

በተመሳሳይ ወቅት ማለትም ታኅሣሥ ዘጠኝ ቀን 1954 ዓ.ም ንጉሱ ቤተመንግሥታቸውን ለአሁኑ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቀድሞ ስሙ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ለሚባለው ለሕዝባቸው ያበረከቱበት ጊዜ ነበር። ይህ የሚያሳየን ንጉሱ ለሀገሪቱ ብቸኛ የሆነውን ዩኒቨርሲቲ ከመክፈት በፊት ለባህር በር ትልቅ ትኩረት ሰጥተው መንቀሳቀሳቸውን ነው።

ለዚህ ኅዳር 23 ቀን 1954 ዓ.ም የአሰብ ወደብ የምረቃ ሥነ ሥርዓት ላይ ንጉሰ ነገሥቱ ባደረጉት ንግግር ነው። « .....በ1916 ዓ.ም ወደ ኤሮፓ የሔድንበት ዋናው ጉዳይ ፤ ኢትዮጵያ በማናቸውም ዓይነት በጭሰኝነት እንኳ ቢሆን የባህር በር እንዲኖራት በነበረን ብርቱ ምኞት ተመርተን ስለነበር፤ በዚያው ጊዜ የኢጣልያ መሪ ከነበሩት ጋር ተነጋግረን በኮንሴሺን ሊሰጠን ታስቦ የነበረው ከጥቂት ሺህ ሜትር ካሬ መሬት የማይበልጥ ነበር። አሁን ግን በእግዚአብሔር ቸርነት ኢትዮጵያ የራሷን ባህርና የራሷን ወደብ ገዥ በሆነችበት፤ ከኢትዮጵያ ተወስዶ የነበረው ተመልሶ የኢትዮጵያ በሆነበት ታሪክ፤ ተመልሶ ታሪክ በሆነበት በዛሬው ጊዜ ከዚህ ቦታ ተገኝተን ይህንን አዲስ የተሰራውን የአሰብን ወደብ ለኢንተርናሽናል ንግድ መርቀን ስንከፍት እጅግ ደስ እያለን ነው። .... »።

በወቅቱ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ የአሰብ ወደብ ተመርቆ ሥራ መጀመርን አስመልክቶ ኅዳር 25 ቀን 1954 ዓ.ም «ወደብ» በሚል ርዕስ ያስነበበው ርዕሰ አንቀጽ የመጨረሻ አንቀጽ እንዲህ ይል ነበር።

«....ለሥልጣኔ መሠረቱ ትምህርት እንደመሆኑ መጠን በአንድ ፊት ዩኒቨርሲቲው፤ በአንድ ፊት ወደቡ፤ ከዚህም በላይ መንገዱ፤ ሕክምናው፤ ኢንዱስትሪውና ፋብሪካው በየቦታው ተደጋግፈው መብቀልና ማደግ ሲጀምሩ ለሥልጣኔአችን ጣዕም በየዕለቱ ለምናደርገው የጋራ ትግል አላማና ፍቺ እያስገኙልን ይሄዳሉ። ....»

ኢትዮጵያ ወደብ እንደሚያስፈልጋት ከታመነና ይህ ሃሳብም በዓለም አቀፍ ሕጎች የሚደገፍ ከሆነ ጥያቄ መነሳቱ የማይቀር ጉዳይ መሆኑ ግንዛቤ ሊያዝ ይገባል። በመወራቱም ግርታ ሊፈጥር አይገባም። ምክንያቱም ሀገሪቷ ካለ ወደብ ጥገኛ ሆኖ መኖርን መምረጥ አይኖርባትምና ነው።

ከዚህ ውጭ ግን አንዳንድ ዓለም አቀፍ ሕጎችና ስምምነቶችም መዳኘት ያለባቸው ወቅቱን ባገናዘበ መልኩ እንጂ የአንድን ወገን ጥቅም ብቻ በሚያስከብር መልኩ መሆን የለበትም። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ከሕዳሴው ግድብ ጋር በተያያዘ የገጠማትን ችግር ማስታወስ ያስፈልጋል።

በግድቡ ግንባታ መጀመሪያ ዓመታት የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት በተለይም ግብጻውያን ሲዘምሩ

**ኢትዮጵያ ወደብ እንደሚያስፈልጋት ከታመነና ይህ ሃሳብም በዓለም አቀፍ ሕጎች የሚደገፍ ከሆነ ጥያቄ መነሳቱ የማይቀር ጉዳይ መሆኑ ግንዛቤ ሊያዝ ይገባል። በመወራቱም ግርታ ሊፈጥር አይገባም**

የነበሩት ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ በቅኝ ግዛት ዘመን የነበረው ስምምነት እንዲተገበር ነበር። በወቅቱም ሆነ አሁንም ድረስ ይህ አግላይና አድሏዊ የሆነን ስምምነት ኢትዮጵያ ተቀብላው ቢሆን ኖሮ የህዳሴው ግድብና ከሱ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ በሀገሪቱ ያለው ሁኔታ ምን ሊመስል እንደሚችል መገመቱ አያዳግትም።

በመሠረቱ በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚገኙ የተጎራበቱ ሀገራት የሚያገናኛቸው በርካታ ነገሮች እንዳሉ ይታወቃል። ዘመኑ ደግሞ ለማንም ቢሆን ድንበር አጥሮ ለመኖር የሚፈቅድ አይደለም። እንኳን ሰደተኛ የምንቀባበል እኛ የአፍሪካ ሀገራት እንቅርና ሌሎቹም ቢሆኑ ድንበራቸውንም ሃሳባቸውንም ለድርድር አልዘጉም።

ኢትዮጵያም ብትሆን ላለፉት ሶስት አስርት ዓመታት በብዙ ምስቅልቅል ውስጥ ሆና እንኳን ከኤርትራ፤ ከሶማሊያ፤ ከደቡብ ሱዳንና ሌሎች ሀገራትም የተሰደዱ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን እጇን ዘርግታ ስትቀበል መኖሯ መዘንጋት የለበትም። ይህ አርቴፊሻል ድንበር ለግንኙነት አልፋ እና ኦሜጋ ለመሰላቸው አንዳንድ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ አካላት ጥሩ ማሳያ ነው።

እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባውና እኛም ሆንን ጎረቤቶቻችን ሊገነዘቡት የሚገባው እነሱ ችግራችን ፍላጎታችን ባሉት ነገር ላይ ብቻ ሳይሆን እኛም በምናነሳቸው ጉዳዮች ላይ ለመወያየት በርን ክፍት ማድረግ መሸነፍ ሳይሆን መሰልጠን መሆኑን ነው።

የታሰቡና የተወሩ ነገሮችን በሙሉ ከጦርነትና ነገር ጫሪነት ጋር ማያያዝም ተገቢ አይደለም። በኢትዮጵያ በኩል መንግሥት ሁሉንም ወገን ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ ያሉትን የሰላም አማራጮች በሙሉ አሟጦ እንደሚጠቀም ይታወቃል።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በእርግጥም ኢትዮጵያም ኢትዮጵያውያንም ወደብ ያስፈልገናል ይገባናልም። በመሆኑም ኢትዮጵያ የባህር በር የማግኘቷ ጥያቄ ትላንት የነበረ ዛሬም ያለ ወደፊትም የባህር በር እስኪታገኝ ድረስ በትውልድ ቅብብሎሽ የሚቀጥል መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

# ነፃ ሃሳብ

## የባህር በር ሰሞንኛ "አጀንዳ" ወይስ የ"ህልውና" ጉዳይ?

**ሰው መሆን**

ዜጎች ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ በሆኑ ምክንያቶች በኢኮኖሚ ጫና ውስጥ እንደሚገኙ እያስተዋልን ነው። ኑሮ አሻቅቧል። ከትንሿ መርፌ እስከ ትልቁ የቅንጦት ቁስ የመግዛት አቅምን ባላገናዘበ ሁኔታ ዋጋው ጣሪያ ነክቷል። አንድ ርምጃ ወደፊት ስንጓዝ ሁለት ወደኋላ የሚመልሱን የኑሮ ውጥንቅጦች እዚህም እዚያም መሰናክል ሆነው ይታያሉ። ጫናው ለመፈጠሩ ከዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ መዛነፍ ጀምሮ እዚህችው አጠገባችን እስካለችው ስንፍና ጭምር ምክንያት አድርጎ ማንሳት ይቻላል።

የዓለም የነዳጅ ዋጋ ማሻቀብ፣ ጦርነት፣ ጫፍ የረገጠ ሙስና፣ የእርስ በእርስ ግጭት፣ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ምክንያቶች ተደራርበው የኢኮኖሚውን ስብራት እያባባሱት ይገኛሉ። የኢኮኖሚ አሻጥር፣ የጥቁር ገበያ፣ ከትርፍ ህዳግ በላይ መሻት፣ የምርት እጥረት፣ የነዳጅ ዋጋ ንረት አሁን እየታየ ለሚገኘው የዋጋ ማሻቀብ (የብር የመግዛት አቅም መዳከም) መሠረታዊ መነሻዎች ቢሆኑም በርካታ ስር የሰደዱ ተጨማሪ ምክንያቶችንም መጥቀስ ይቻላል።

መንግሥት ከላይ ባነሳናቸውና በሌሎች ምክንያቶች የሚፈጠሩ የኢኮኖሚ ጫናዎች መፍትሔ ለመስጠት እየሰራ ነው። የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት፣ ድጎማ፣ የፖሊሲና ሕግ ማሻሻያ እንዲሁም ጠንካራ የሥራ ባህል ለመፍጠርም ይሰራል። በኢኮኖሚ እድገትና በዜጎች የኑሮ መሻሻል ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ ለማምጣት የሚረዱ ታላላቅ ፕሮጀክቶች (የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ ዘመናዊ ግብርና፣ ኢንዱስትሪ መንደሮች) ለማስፋፋት ቢተጋም ዘላቂ እድገትና የተረጋጋ ኢኮኖሚ ለመፍጠር ይህ ብቻ በቂ አይሆንም።

ኢትዮጵያ በ2030 ዓ.ም 150 ሚሊዮን ይደርሳል ተብሎ የሚታሰበውን ሕዝብ አብዛኛውን መሠረታዊ ፍላጎት የምታሟላው በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ከውጭ በማስገባት "import" በማድረግ ነው። በቁጥር ከሚጠቀሱ ጥራጥሬና የቅባት እህል፣ ቡና፣ አበባ (horti-culture) ምርት እንዲሁም ወርቅን ከመሳሰሉት ማዕድናት ውጭ "ይህ ነው የሚባል"! ለቁጥር የሚሞላ ምርት አትልክም፤ ወይም "export" አታደርግም። ይህ መሆኑ ከላይ ከጠቀስናቸው ምክንያቶች በተጨማሪ ለኑሮ ማሻቀብና ለከፍተኛ የንግድ ሚዛን መዛባት የሚዳርግ ነው።

እውነቱን ለመናገር ከ90 በመቶ በላይ የሚሆነው ፍላጎቶቻችንን የምናሟላው በከፍተኛ ምንዛሬ ገቢ ማድረጋችን ከላይ በመግቢያችን ላይ ከጠቃቀስናቸው የኑሮ ውድነትን ከፈጠሩ ምክንያቶች በባሰም ሁኔታ ጫና የሚፈጥር እንደሆነ እንድንገነዘብ ያስገድደናል። ይህ ጉዳይ ከድጡ ወደ ማጡ የሚሆነው ደግሞ ሀገራችን ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ሀገር መሆኗን ስናስብና የምትገዛቸውን ምርቶች በጎረቤት ሀገሮች ይሁንታና በኪራይ ወደብ ማስገባቷን ስንመለከት ነው።

እዚህ ጋር ስንደርስ ነው ኢትዮጵያ የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ የሚያሻሽሉ፣ አሁን የተፈጠረውን ጊዜያዊ የኢኮኖሚ ጫና የሚቀንሱ፣ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን የሚተኩ ፕሮጀክቶችንና የልማት እቅዶችን ከመተግበር ባሻገር ጠንካራ የውሃና የወደብ ፖሊሲ እንደሚያስፈልጋት የምንገነዘበው። ይህንን ጉዳይ በቅጡ መገንዘብ እንዲያስችለን "የወደብ ጉዳይ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ለምን ቁልፍ ጥያቄ ሊሆን ይችላል" የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ እንደሚከተለው ለመመለስ ይሞክራል።

ከላይ አስምረንበት እንዳለፍነው ከመቶ ሚሊዮን ተሻግሮ ወደፊት እየገሰገሰ ለሚገኘው የኢትዮጵያ ሕዝብ መሠረታዊ ፍላጎት መሟላት በራስ አቅም አይቻልም። ይህ ደግሞ የግዴታ ወደ ውጭ እንድናማትር ያስገድደናል። በአጭር ጊዜ ውስጥ ሁሉንም ፍላጎቶች በራስ አቅም መተካት ካልተቻለ ደግሞ እስካሁን እያደረግነው እንዳለው ወደብ ተከራይተን ከፍተኛ ወጪ እያወጣን ማስገባት ሊኖርብን ነው። ይህ ደግሞ በሚከተሉት ምክንያቶች በዘላቂነት አያዋጣንም።

### የንግድ መስመሮች

ኢትዮጵያ ወደብ የሌላት ሀገር በመሆኗ ብቻ ከሶስት አስርት ዓመታት ለዘለቀ ከፍተኛ ወደብ አገልግሎት ወጪ ሲያጋጥማት ቆይቷል። ይህ ብቻ ሳይሆን ለወጪና ለገቢ የንግድ መስመሮች በጎረቤት ሀገሮች ጥገኛ እንድትሆን አስገድዷታል። የመርከብ መንገዶችን እና ወደቦችን በቀላሉ ማግኘት ካልተቻለ ዕቃዎችን ማጓጓዝ የበለጠ ውድ እና ጊዜ የሚወስድ ጉዳይ ነው። ይህ ደግሞ የንግድ ሥራ ወጪን ከፍ ከማድረጉም በላይ የኢኮኖሚያዊ እድገቶችን፣ እድሎችን እየገደበ ይገኛል። የዚህን ውጤት በቀጥታም እያንዳንዱ ዜጋ ላይ በየጊዜው እንመለከተዋለን።

ምርትን የማስመጣት እና የወጪ ንግድ የሚያሳልጠው ወደብ አለመኖር (import, ex-port goods) የጎረቤት ሀገራት ጥገኛ ከማድረጉና ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ከመጠየቁ ባሻገር ወደብ የሌላት ኢትዮጵያ አየር ወይም ባቡር ባሉ ውድ የመጓጓዣ ዘዴዎች ላይ ብቻ እንድትተማመን እያስገደዳት ይገኛል። ይህ ደግሞ የንግድ ሥራ ወጪን ከፍ በማድረጉ ምክንያት የኢኮኖሚያዊ እድገትን እየገደበ ነው። ዓለም ላይ ካለው ያልተረጋጋ የዋጋ ትመናና ማሻቀብ ጋር የእነዚህ ወጪዎች መደራረብ ሲደበር አሁን እየተፈጠረ ላለው ኢኮኖሚያዊ ውጥንቅጥ ምክንያት ይሆናል።

ኢትዮጵያ ቀጥተኛ የወደብ ተጠቃሚ ባለመሆኗ ምክንያት የኢኮኖሚና የልማት እድገት ላይ የሚፈጥረው ችግር ከላይ ያነሳሁት ብቻ አይደለም። ከእርሱ በተጨማሪ የኢትዮጵያ የወደብ ተጋሪ አለመሆን በዓለም አቀፍ ንግድ ውስጥ ለመሰማራት እና ዓለም አቀፍ ገበያዎችን ለመድረስ ፈተናዎች እየጋረጠባት ይገኛል።

ለዓለም አቀፍ ንግድ ያለን ተደራሽነት ውስን ከመሆኑም በላይ የንግድ ሽሪክ ሀገሮችና ታላላቅ ካምፓኒዎች ጋር እንዳንወዳጅ እድሉን አጥብቦብናል። የባህር ላይ ቀጥተኛ መዳረሻ ስለሌለ ኢትዮጵያውያን ራቅ ካሉ ሀገሮች ጋር አዲስ የንግድ ግንኙነት ለመመስረት ውስብስብ መስመሮችንና አስቸጋሪ መንገዶችን የግዴታ መከተል ይኖርብናል።

መዛግብት እንደሚያስረዱን የባህር ንግድ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ወደቦች በሀገሮች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እድገት ውስጥ ማዕከላዊ ሚና ይጫወታሉ። ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነው የዓለም የሸቀጥ ንግድ (በመጠን) የሚጓጓዘው በባህር መንገዶች ነው። በኮንቴይነር የሚጓጓዙ ምርቶች ማረፊያ ደግሞ ወደቦች (የባህር በር) ናቸው። ለልዩ ልዩ ፍላጎቶች የሚውሉ እነዚህ ቁሶች ደህንነታቸው ተጠብቆና ጥራታቸው ሳይጓደል ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ የኢትዮጵያ መንግሥት በነፃነት ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆን ይገባዋል።

በተመሳሳይ በሀገር ውስጥ ተመርተው ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን በወደብ እንቅስቃሴ ላይ የሚኖረውን የጥራት ሂደት መከታተል ያስፈልጋል። ይሁን እንጂ ሀገሪቱ ወደብ አልባ (landlocked) በመሆኗ ምክንያት ፍላጎታችንን ለማስፈፀም ውስብስብ ሂደቶችን የግዴታ መከተል ይኖርብናል።

ወደብ አልባ መሆን የሀገርን አማካይ እድገት በ1 ነጥብ 5 በመቶ ድረስ (አሃዙ በጥናቶች ላይ የተለያየ ቢሆንም) በዓመት እንደሚቀንስ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ይናገራሉ። ውጤታማ ያልሆኑ የወደቦች አገልግሎቶችንና የእቃ ማጓጓዝ ሂደቶች አሰራር በማዘግየት አቅምን ይቀንሳሉ። ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነን መንግሥት የሀገር ውስጥ ፍላጎቶችን በግዥ ለማስገባት በሚሞክርበት ጊዜ በቢሮክራሲና በልዩ ልዩ ምክንያቶች ወደብ ላይ ተቀምጠው ረጅም ጊዜ የሚቆዩ ምርቶች (እንደ ማዳበሪያ፣ ስንዴና ሌሎችም ሸቀጦች) ስንመለከት ነው። ወደ ውጭ የሚላኩትም ቢሆኑ ወደብ ላይ በመቆየታቸውና ጥራታቸው (export stand-ard) በመጓደሉ ምክንያት ለኪሳራ መዳረጋቸው አይቀርም።

### ወደብ ቢኖረን...

የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ኢትዮጵያ የወደብ ባለቤት ብትሆን (አፈፃፀሙንና የህግ ሂደቱን ለጊዜው እንተወውና) አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ እየተፈጠረ ያለውን ኢኮኖሚያዊ ጫና በግማሽ እንደምትቀንስ ያምናል። ወደብ በትክክል ከተሰራና ከተመራ በምርት እና ሥርጭት ሥርዓቶች ላይ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ፣ የማኑፋክቸሪንግ፣ የሎጂስቲክስ እድገትን ለመደገፍ፣ የሥራ እድል ለመፍጠር እና የገቢ አማራጮችን ለማስፋት ያግዛል።

ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ እንደ አለመታደል ሆኖ የባህር በር ከሌላቸው ታዳጊ ሀገራት ተርታ የምትመደብ መሆኑና የባህር ወደብ ባለመኖሩ ብዙ ዋጋ እየከፈለች ነው። ዜጎቿ በዚህ ምክንያት ብዙ እድል አጥተዋል። የንግድ ህልውናችን የሚወሰነው በሌሎች ሀገሮች ወደብ ላይ ነው። የመጓጓዣ አገናኝ የግብይት ወጪዎች ከፍ ያለ በመሆኑ እቅሙን ለተጨማሪ ልማትና ኢንቨስትመንት እንዳይውል ተገድደናል።

ወደብ ቢኖረን በዓለም አቀፍ የአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ አስፈላጊ አንጓዎች የምንላቸውን ሸቀጦችን የሚይዙ የኮንቴይነሮችንና ልዩ ልዩ የወደብ አገልግሎቶችን በቀላሉ በትንሽ ወጪ መቆጣጠር ያስችለናል። በተለይ ለኢኮኖሚ ዲፕሎማሲና ለንግድ ሽርክና የድርድር አቅምን የሚያሳድገው ወደብ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ወደቦች ለብዙ ታዳጊ ኢኮኖሚዎች "የእድገት ስትራቴጂ" ተደርገው ይወሰዳሉ፤ ወሳኝም ናቸው።

ከፍተኛ ጥራት ያለው የወደብ መሠረተ ልማት ዝርጋታ ቢኖረንና በብቃት የሚሰራ ቢሆን ለእድገት ስትራቴጂዎች ተፈፃሚነት በተለይም የወጪ ንግድ ገበያውን ለመምራት ድርሻው የላቀ ይሆናል።

### እንደ መውጫ

እኛ ኢትዮጵያውያን በኢኮኖሚው ረገድ ፈቀቅ እንድንል፤ የልማት አጀንዳዎቻችንን በተገቢው ለማስፈፀም ቀጥተኛ የወደብ ተጠቃሚ መሆን እንደሚገባን ማመን ይኖርብናል። "እንዴት እናስፈፅመው" የሚለውን ለሕዝብ ውይይት፣ ለዓለም አቀፍ ሕጎችና ለወከልነው መንግሥት በኃላፊነት እንተወው። በመሠረታዊነት ግን "ወደብ የአንድ ሰሞን የፖለቲካ አጀንዳችን ሳይሆን የህልውና ጉዳያችን" መሆኑን በአግባቡ መረዳት ይኖርብናል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መንግሥት ይህንን ጉዳይ ወደ መድረክ አምጥቶ የመወያያ ርዕስ ማድረጉን እናስታውሳለን። ጉዳዩን በሚገባ ካለማጤን አሊያም በስሜታዊነት ተነሳስተን ሰሞነኛ አጀንዳ ብቻ እንደሆነ ማሰባችን ግን የዚህ ርዕስ ነገር ፀሐፊ አያምንበትም።

አጀንዳውን ያንሸራሸረውም ይሁን ጉዳዩን አንሸዋርሮ የተረዳው አካል አንድ ቁልፍ የሆነ ጉዳይ ማወቅ ያለበት የባህር በር ባለቤት መሆን ለዛሬ ሳይሆን ለነገ የኢትዮጵያ ህልውና መሠረት ነው። ለዚህ ነው ጠቅላይ ሚኒስትሩ "ዛሬ ላይ ባናስፈፅመውም እስከናሳካው ድረስ አጀንዳችን ሆኖ ልንወያይበት ይገባል" ማለታቸው ። ሰላም!!

> **ወደብ ቢኖረን በዓለም አቀፍ የአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ አስፈላጊ አንጓዎች የምንላቸውን ሸቀጦችን የሚይዙ የኮንቴይነሮችንና ልዩ ልዩ የወደብ አገልግሎቶችን በቀላሉ በትንሽ ወጪ መቆጣጠር ያስችለናል**

# የቡና ልማትና የገበያ አቅርቦት እድገት - በኦሮሚያ ክልል

**ፍሬሕይወት አወቀ**



ኢትዮጵያ ቡናን ጨምሮ ለተለያዩ የግብርና ምርቶች በሚሆን የአየር ንብረትና ለም መሬት የታደለች ናት፡፡ በቡና መገኛነቷ ትታወቃለች፤ በቡና ምርቷም ከቀዳሚዎቹ ተርታ ትሰለፋለች፡፡ እነዚህ ሁሉ በቡና ዘርፍ ትልቅ አቅም እንዳላት ይመሰክራሉ።

ቡና ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ጉልህ አስተዋጽኦ በማበርከት ይታወቃል፡፡ የኢኮኖሚው የጀርባ አጥንት ሆኖም ነው የኖረው፤ ዛሬም ቡና ለሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ወሳኙ ሰብል ሆኖ ቀጥሏል፤ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንም በቡና እሴት ሰንሰለት ውስጥ በመሥራት ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛሉ፡፡ በአሁኑ ወቅትም ቡና በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መስተጋብር ላይ እያሳደረ ያለውን አበርክቶ ከፍ ማድረግ እንዲቻል እንደ ሀገርም ቡና በሚለማባቸው ክልሎች ደግሞ እንደ ክልል በቡና ልማት ላይ በስፋት እየተሠራ ነው፡፡

የቡና ልማትን በማስፋት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በሀገሪቱ የተለያዩ ክልሎች በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ሲሆን፤ ከእነዚህ ክልሎች መካከልም አንዱ የኦሮሚያ ክልል ነው፡፡ ክልሉ ከሀገሪቱ የቡና ምርት አብዛኛው ይመረትበታል፡፡ በዛሬው የግብርና አምዳችንም በክልሉ የቡና ልማትን ለማስፋፋት እየተሰራ ያለውን ሥራ ለማሳየት ከክልሉ ግብርና ቢሮ የቡናና ሻይ ልማት ዳይሬክተር አቶ ተስፋዬ አቦሴ ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡

አቶ ተስፋዬ እንደሚሉት፤ የኦሮሚያ ክልል በተፈጥሮ የታደለና ለቡናም ሆነ ለሻይ ምርት ምቹ ሁኔታ አለው፡፡ ቡና በክልሉ በሰፊው የሚለማ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በትኩረት እየተሰራበት ይገኛል። አጠቃላይ የኦሮሚያ ክልል በተለይ ለቡና ልማት እጅግ ተስማሚ ኢኮሎጂ አለው፡፡

አርሶ አደሩ ቀደም ሲል ጀምሮ ማንም ሳይነገረውና ኤክስቴንሽኑ ሳይደግፈው ቡናን ሲያለማ እንደነበር አቶ ተስፋዬ አስታውሰው፤ የቡና ኤክስቴንሽን ከተጀመረ ወዲህ ደግሞ የቡና ልማትና የገበያ አቅርቦቱ ከዓመት ዓመት እያደገና እየሰፋ መምጣቱን ተናግረዋል፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ በአሁኑ ወቅት በኦሮሚያ ክልል ከፍተኛ መጠን ያለው ቡና ለማልማት በርካታ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ በተያዘው በጀት ዓመት ብቻ በክልሉ ሁለት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በቡና ተሸፍኗል፡፡

ሁሉም የቡና ችግኞች በተለያዩ ምክንያቶች ምርት የሚሰጡ አለመሆናቸውን የገለጹት አቶ ተስፋዬ፤ ከሁለት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ አንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር ያህሉ ምርት የማይሰጥ መሆኑ ተረጋግጧል ይላሉ፡፡ በመሆኑም ምርት የሚሰጠው መሬት በየዓመቱ እያደገ እንዲመጣ መሠራቱን ተከትሎ ለውጥ እየተገኘ መሆኑን ጠቅሰው፣ ለዚህም ዋናው ምክንያቱ የተተከለ ቡና ምርት መስጠት የሚጀምረው ከአራትና አምስት ዓመታት በኋላ በመሆኑ ነው ብለዋል፡፡ ለዚህም ነው በቡና የተሸፈነ መሬት ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ ምርት ወደ መስጠት የሚገባ በመሆኑ የቡና ምርት በየዓመቱ እያደገ የሚሄድ ነው ብለዋል፡፡

በ2015 የምርት ዘመን በኦሮሚያ ክልል 10 ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ኩንታል ቡና መመረቱን ያስታወሱት አቶ ተስፋዬ፤ በተያዘው 2016 በጀት ዓመት 11 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ቡና ለማምረት የቅድመ ዝግጅት ሥራ መሠራቱን ገልጸዋል፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ ይህን ዕቅድ ለማሳካትም በክልሉ በሚገኙ በሁሉም ወረዳዎች የክትትል ሥራው ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ በዚህም የቡና ምርት በየዓመቱ እየጨመረ መጥቷል፡፡ በቀጣይም ምርትና ምርታማነቱ እያደገ የሚሄድ ይሆናል፡፡

በበጀት ዓመቱ በክልሉ ለማምረት የታቀደውን 11 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ቡና መሰብሰብ እንዲቻል የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች መሠራታቸውን የገለጹት አቶ ተስፋዬ፤ በዋናነት ቡናው ደርሶ ሲሰበሰብ በጥራት መሰብሰብ የሚቻልበት ምቹ ሁኔታ መፈጠሩን ገልጸዋል፡፡ ለዚህም ከክልሉ ጀምሮ እስከታችኛው መዋቅር ድረስ የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል ብለዋል፡፡ በዋናነትም በቡና ልማት ዙሪያ ያለውን ችግር በመለየት ከቡናና ሻይ ባለሥልጣን ጋር ውይይት መደረጉንም አመላክተዋል፡፡

ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ ባለፈ ቡናው ደርሶ በሚሰበሰብበት ወቅትም ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልግ የጠቀሱት አቶ ተስፋዬ፤ በአሰባሰብ ሂደትም እንዲሁ ውይይቱን ወደ ዞን፣ ቀበሌና ወረዳ በማውረድ ቡናው ሲደርስ እንዴት መሰብሰብ እንዳለበት መግባባት ላይ መደረሱን ተናግረዋል። ቡናው ከተሰበሰበ በኋላም እንዴት መድረቅ እንዳለበት እየተሰራ ነው ያሉት አቶ ተስፋዬ፤ በዚህም በየጊዜው ለውጥ እየተመዘገበና የሚፈለገው የቡና ጥራትና ዕድገት እየመጣ ነው ብለዋል፡፡

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ የቡና ምርትን ለማሳደግ በዋነኛነት ጥራቱን ለማስጠበቅና ቡና እንዳይባክን ለማድረግ ሁሉን አቀፍ ውይይት ማድረግ ያስፈልጋል። ከአርሶ አደሩ በተጨማሪ ከህብረት ሥራ ማህበራት ጋርም እንዲሁ በስፋት እየተሰራ ይገኛል። ከአርሶ አደሩ በተጨማሪ የህብረት ሥራ ማህበራቱ አባሎቻቸውን ጨምረው በመሳተፍ ጥራቱን የጠበቀ ቡና እንዲመረትና ብክነት እንዳይፈጠር ቡናውን በጥራት ሰብስበው ለገበያ እንዲያቀርቡ በማድረግ ሁሉን አቀፍ ምክክር እየተደረገ ነው፡፡

የቡና ምርት መጠንን ከፍ ለማድረግ ጥራቱ ላይ መሥራት አንዱና ወሳኝ ጉዳይ ነው የሚሉት አቶ ተስፋዬ፤ ጥሩ ቡና ከተመረተና በጥራት መሰብሰብ ከተቻለ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እንደሚቻል ነው ያስረዱት፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ አርሶ አደሩ የቡና ዋጋ ወደቀ ሲባል በጥራት የማምረትና የመሰብሰብ አሰራሩን ቀንሶ ተስፋ ይቆርጣል፡፡ በዚህ ጊዜ እንደፈለገ ይሰበስባል፤ ትኩረት አድርጎ የማምረትና የመሰብሰብ ፍላጎቱም ይቀንሳል፡፡ ስለዚህ ቡናውን በጥራት ሰብስቦ ጥሩ ዋጋ እንዲያወጣ መሥራት ያስፈልጋል፡፡

በጥራት የተመረተና የተሰበሰበ ቡና ደግሞ ጥሩ ገበያ ያገኛል ያሉት ዳይሬክተሩ፣ ይህም አርሶ አደሩን ተጠቃሚ እንደሚያደርገው ነው የገለጹት። አርሶ አደሩ ላመረተው ቡና ጥሩ ዋጋ ሲያገኝ በቀጣይ የማምረትና በጥንቃቄ የመሰብሰብ ፍላጎቱ እንደሚጨምርም ገልጸዋል፡፡ በዚህ መልኩ እንዲሰራ የማበረታታት፣ የመደገፍና የመከታተል ሥራን አጠናክሮ መሥራት አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በክልሉ ሌሎች የአመራር ሥራዎችም ተጠናክረው መቀጠላቸውን የጠቀሱት አቶ ተስፋዬ፤ ለአብነትም በማሳ እንክብካቤዎች ላይ አርሶ አደሩ በትክክል እንዲሰራ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ሌላው ለምርትና ምርታማነት እንዲሁም ለቡና ጥራት እንደ ኦሮሚያ ክልል ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራው ያረጁ ቡናዎችን መጎንደል መሆኑንም አቶ ተስፋዬ አስታውቀዋል፡፡

ዳይሬክተሩ እንዳብራሩት፤ እንደ ኦሮሚያ ክልል በአብዛኛው የሚገኙት የቡና ዛፎች ያረጁና ከ60 እስከ 70 ዓመት ዕድሜን ያስቆጠሩ ናቸው፡፡ ይህ ዓይነቱ ያረጀ ቡና ጥራት ላይ በሚያሳድረው ተጽዕኖ ምክንያት በምርትና ምርታማነት ላይም እንዲሁ በጣም የወረደ አፈጻጸም ነው የሚያሳየው፡፡ ስለዚህ የመጎንደል ሥራው በየዓመቱ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

የቡና ጉንደላ ሥራ በክልሉ በየዓመቱ የሚከናወን ሥራ ቢሆንም፣ ተጎንድሎም ውጤታማ የማይሆን የቡና ተክል በመኖሩ በቦታው ላይ ሌላ የቡና ችግኝ እንዲተካ የሚደረግበት ሁኔታም አለ፡፡ ቡናን በየዓመቱ በመጎንደል ጥራትና ምርታማነትን ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል፡፡ በዚህም ባለፈው በጀት ዓመት ብቻ በ136 ሺ ሄክታር መሬት ላይ የሚገኝን የቡና ተክል የመጎንደል ሥራ ተሰርቷል፤ ምርት የማይሰጡትን የመተካት ሥራም ተከናውኗል፡፡

በተያዘው በጀት ዓመት ደግሞ ከዚህ በበለጠ ለመሥራት ታቅዷል፡፡ ይህንንም ጊዜው ሲደርስና ቡናው ከተሰበሰበ በኋላ ለመሥራት የታቀደ ሲሆን፤ በዕቅዱ መሠረት ለመሥራትም የቅድመ ዝግጅት ሥራቸውን ተጠናቅቀዋል፡፡

ቡና ተተክሎ ከአራትና አምስት ዓመታት ቆይታ በኋላ ምርት እንደሚሰጥ የጠቀሱት አቶ ተስፋዬ፤ የተጎነደለ ቡና ግን ከሁለት ዓመት በኋላ ምርት እንደሚሰጥ ነው የተናገሩት፡፡ ይህም አርሶ አደሩን እንደሚጠቅም ጠቅሰው፣ እዚህ ላይ በስፋት እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል፡፡ ይህንንም አርሶ አደሩ በከፍተኛ ተነሳሽነት እንደሚተገብረው ገልጸው፣ በተለይም ባለፈው በጀት ዓመት አብዛኛው አርሶ አደር በስፋት የሄደበትና ከታቀደው በላይም የሠራበት መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ ይህም አርሶ አደሩ ችግሩን በሚገባ የተረዳው እንደሆነ ያመላክታል ብለዋል፡፡ እንደ ኦሮሚያ ክልል አጠቃላይ ያረጁ ቡናዎች እየተጎነደሉ መሆናቸውንም ጠቁመዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ በክልሉ ከሚገኙ 290 ወረዳዎች መካከል 193 ወረዳዎች ቡና የሚያመርቱ ናቸው፡፡ ከ21 ዞኖች መካከል በ18 ዞኖች ቡና ይመረታል፡፡ ከአንዱ ዞን ሌላኛው ዞን በመጠን የሚበላለጥ ይሁን እንጂ በአብዛኛው በክልሉ በሚገኙ ወረዳዎችና ዞኖች ቡና ይመረታል፡፡ ከዚህ ቀደም ቡና የማይመረትባቸው እንደ ሸዋ ያሉ አካባቢዎች አሁን አሁን ቡና ማምረት ጀምረዋል፡፡

በቡና ልማት ቀደም ሲል ጀምሮ ይታወቁ የነበሩ አካባቢዎች ስለመኖራቸው ያነሱት አቶ ተስፋዬ፤ ነባር ቡና አምራቾች በሀገሪቱ ምዕራብ አካባቢዎች በጅማ፣ በደሌ፣ በኢሉባቦር፣ በወለጋ፣ ምዕራብና ምስራቅ ጉጂ ዞኖች ቡና በስፋት እንደሚመረትና ከዓመት ዓመት የምርት መጠናቸውም እየጨመረ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ በተጨማሪም በምዕራብ አርሲ ነንሰቦ ወረዳም እንዲሁ በከፍተኛ መጠን ቡና እንደሚመረት ጠቁመው፣ በዚህ አካባቢ የሚመረተው ቡና በተለየ ሁኔታ በውጭ ገበያ ተፈላጊ እንደሆነም ነው ያስረዱት፡፡

በክልሉ ቡና በአብዛኛው በአርሶ አደር እንደሚለማ የጠቀሱት አቶ ተስፋዬ፤ በኢንቨስትመንት መሬት ወስደው ቡናን የሚያመርቱ ጥቂት ባለሃብቶች እንዳሉም ገልጸዋል፡፡ በሀገሪቱ ከሚመረተው 95 በመቶ ያህሉ ቡና በኦሮሚያ ክልል በአርሶ አደር አማካኝነት እንደሚመረትም ጠቅሰዋል፡፡

የቡና ሻይ ባለሥልጣን በበኩሉ በ2016 በጀት ዓመት እቅድ ላይ ውይይት ባደረገበት ወቅት ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ በቡና ዘርፍ ከፍተኛ ለውጥ እየታየ መሆኑን የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አዱኛ ደበላ (ዶ/ር) ገልጸዋል፡፡ ከቡና ምርት ባለፈ በኤክስፖርት ግኝትም ከፍተኛ ውጤት እየተመዘገበ መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህ ውጤት የተመዘገበው ከሁሉም ክልሎች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እና በመናበብ መሥራት በመቻሉ እንደሆነ አመላክተዋል፡፡

የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ድርሻም እጅግ ከፍተኛ መሆኑን የጠቀሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በተያዘው በጀት ዓመት 350 ሺ ቶን ቡና ለውጭ ገበያ በማቅረብ አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ እየተሠራ እንደሆነ ተናግረዋል። ዕቅዱን ለማሳካትና የቡና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የኤክስፖርት ገቢውን ወደላቀ ደረጃ ለማድረስ በዘርፉ ያሉ እድሎችን በሙሉ አሟጦ መጠቀም እንደሚገባም አሳስበዋል፡፡

በቡና ብቻ ሳይሆን በሌሎች የግብርና ልማት ሥራዎችም ኢትዮጵያ ምቹ ሁኔታና ተስማሚ የአየር ንብረት እንዳላት የጠቀሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ከቡና በተጨማሪ በተለያዩ አካባቢዎች ባሉ ወረዳዎች የቅመማ ቅመም ምርት በስፋት እየተመረተ እንደሚገኝና የልማት ሥራውም ተጠናክሮ መቀጠሉን ገልጸዋል። ይህም ከቡና ቀጥሎ የሀገሪቱን የኤክስፖርት ግኝት በማሳደግ ኢኮኖሚውን በመደገፍ ትልቅ አቅም ሊፈጥር እንደሚችልም ነው ያብራሩት። ለዚህም መንግሥትን ጨምሮ መላው የተቋሙ ሠራተኞች በመንግሥት የተጣለባቸውን ኃላፊነት ለመወጣት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ መነሳሳት የፈጠሩበት ጊዜ እንደሆነም አመላክተዋል፡፡

ማህበራዊ

# አስኳላ

# ናሽናል አቪዬሽን በግሥጋሴ ጎዳና

ግርማ መንግሥቴ

በኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ቀደም ያለ ታሪክ ቢኖረውም ብዙም አልተስፋፋም። በተለይ ከአፍሪካ አህጉር አኳያ ሲታይ ታሪኩ ቢጎላም አሰራርና እድገቱ ቀርፋፋ ብቻ ሳይሆን አንዳንዴ የኋሊትም ይመለሳል፡፡ ለዚህ ደግሞ አሁን የሚታየው የትምህርት ጥራት ጉድለት እንደምክንያት ይጠቀሳል፡፡

የቀድሞው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ የዛሬው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከራሱ አልፎ በርካታ አፍሪካዊ ልሂቃንን እስከ ማፍራት ድረስ ዘልቆ እንደነበር ከበቂ በላይ ተመስክሮለታል። በርካታ አፍሪካዊ ሀገራት መሪዎችን ማፍራቱ ሁሉ በበርካታ ሰነዶች እማኝነት ተረጋግጦለታል፡፡

የመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብዛት በአጭር ጊዜ ውስጥ ተስፈንጥሮ 50 አካባቢ ደርሷል። ይህም ዩኒቨርሲቲዎችን ብቻ ያካትታል። የጥራት ችግር ቀስ ብሎ የሚመጣ መሆኑ ከግምት ውስጥ ገብቶ የዩኒቨርሲቲ ቁጥር ማሻቀብ ዋጋ እያስከፈለ ይገኛል። እንዲያም ሆኖ የትምህርት ሚኒስቴር "ለለውጥ እየተጋሁ ነው" ባለው መሠረት እየሰራ ከሆነ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ለውጥ ይመጣል ተብሎ ይታሰባል።

ወደ ግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሲመጣም ተመሳሳይ ችግር ይታያል፡፡ እንደውም በእነዚህ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ችግሩ ብሷል። ተቋማቱ እንደ ፋሽን ቀሚስና ሱሪ የአንድ ሰሞን ዩኒቨርሲቲዎች በመሆን ብቻ ከጥቂት ዓመታት በኋላ እየከሰሙ ከመሄድ አላመለጡም። ሥራቸውም አስተምሮ ማስመረቅ ሳይሆን ዲግሪና ዲፕሎማ እያሳተሙ መቸብቸብ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ይህም አሁን ላይ ሀገርን ከፍተኛ ዋጋ እያስከፈለ ነው፡፡ ከነዚህ ተቋማት ዲግሪና ዲፕሎማ የተቀበሉትንም የሥነ ልቦናና ሌሎችም ጉዳቶች እያደረሰባቸው ይገኛል፡፡ በተለይም ከሰሞኑ በየተቋማቱ "የትምህርት ማስረጃን ማጣራት።ጋር በተያያዘ እየታየና እየተሰማ ያለው ጉድ ለሰሚም ሆነ ለተመልካች ግራ ያጋባል፡፡

ነገር ግን በተናጠል ማየት ከተቻለ አሁንም በጥሩ ሁኔታ እየሄዱ፣ ከራሳቸውም አልፈው ለሌላውም እየተረፉ ያሉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አሉ። ከነዚህ ውስጥ አንዱ ናሽናል አቪዬሽን ኮሌጅ ነው። ኮሌጁ ባለፈው ቅዳሜ 943 ተማሪዎቹን ያስመረቀ ሲሆን፣ በምረቃ ሥነ ሥርዓቱ ላይ የኮሌጁ አጠቃላይ እንቅስቃሴና የመጣበት መንገድ በኮሌጁ ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ደርበው በለው አማካኝነት ተገልጿል፡፡

ናሽናል አቪዬሽን ኮሌጅ በድህረ ምረቃ፣ በቅድመ-ምረቃ፣ በTVT (ቴክኒክና ሙያ እና በሰርተፊኬት ፕሮግራሞች ያሰለጠናቸውን ተማሪዎች ለአስረኛ ዙር ጥቅምት 17 ቀን 2016 ዓ.ም በስካይ ላይት ሆቴል በደማቅ ሥነ ሥርዓት አስመርቋል።

ኮሌጁ የናሽናል ኢንቨስትመንት ግሩፕ አባል እና የናሽናል አየር መንገድ (National Airways) እህት ኩባንያ ሲሆን፣ ሀገራችን በአቪዬሽን፣ በሆቴልና ቱሪዝም እያደገ የመጣውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት ከማሟላት አኳያ በሚሰጣቸው መርሃ ግብሮች አማካኝነት ብቁ ሙያተኞችን በማፍራት ለዘርፉ እድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ከሲቪል አቪየሽን ባለሥልጣን እውቅና ባገኘበት በአውሮፕላን ጥገና ቴክኒሺያንነት (Aviation Maintenance Technician) ተማሪዎችን ተቀብሎ ማሰልጠን የጀመረ፣ በሀገሪቱ ብቸኛ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው።

በምረቃ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ እንደተገለፀው፣ ናሽናል አቪዬሽን ኮሌጅ በቅርቡ ናሽናል ዩኒቨርሲቲ የመሆን አላማን ሰንቆ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። ከዚሁ አዲስና ትልቅ ግብ ጋር በተያያዘ ኮሌጁ የስልጠና ዘርፎችን በማስፋት በጤናው ዘርፍ፣ በነርሲንግና በፋርማሲ ስልጠና መስጠት ጀምሯል፡፡ በእለቱ በተሰጠው መግለጫ ላይ እንደተነገረው፣ ስለ ናሽናል አቪዬሽን ኮሌጅ ሲነሳ ናሽናል አየር መንገድን ማንሳት ግድ ይላል።

ኮሌጁ ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ደርበው በለው እንደተናገሩት፣ ናሽናል አየር መንገድ በኢትዮጵያ



ኮሌጁ ለ10ኛ ዙር 943 ተማሪዎችን ከሳምንት በፊት አስመርቋል፣

በአየር ትራንስፖርት ዘርፍ ከሚንቀሳቀሱ የግል አየር መንገዶች መካከል ግንባር ቀደም ሲሆን፣ ደህንነቱ የተጠበቀና አስተማማኝ የመንገደኛና የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት፤ በእድገት ግስጋሴ ላይ የሚገኝ ግዙፍ ተቋም ነው፡፡

አየር መንገዱ በሀገራችን በፍጥነት እያደገ የመጣውን የአቪዬሽን፣ የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፎች ተወዳዳሪነት በዘላቂነት ለማሳደግ ለሀገራዊ ልማቱ የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማበርከት ጉልህ ድርሻ ያለውን የሠለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት ከ10 ዓመት በፊት የራሱ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሆነውን ናሽናል አቪዬሽን ኮሌጅ አቋቋመ።

ናሽናል አየር መንገድ ከተቋቋመ ጀምሮ በሀገር ግንባታ ላይ ተሳታፊ እየሆነ መጥቶ በልዩ ልዩ ዘርፎች ላይ እየተሳተፉ ያሉ 10 የሚሆኑ ድርጅቶች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኗል። ከአንድ ዓመት በፊት እነዚህ 10 ኩባንያዎችን ለማስተዳደር አመቺ በሆነ መልኩ በናሽናል ኢንቨስትመንት ግሩፕ (NIG-Holding Company) ጥላ ስር ሆነው ተዋቅረዋል። በአሁኑ ጊዜ በናሽናል ኢንቨስትመንት ግሩፕ ሥር በተዋቀሩ ራስ ገዝ ድርጅቶች በቴክኖሎጂ፣ በአየር ትራንስፖርት፣ በግብርና፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋም፣ በአቪዬሽን፣ በሆቴልና ቱሪዝም፣ በማማከርና ጥናት፣ በአጠቃላይ ንግድ፣ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ እንዲሁም በቴሌኮም አገልግሎት ላይ ተሰማርቶ ለሀገርና ለወገን የሚጠቅሙ ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል። (የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት በናሽናል ኢንቨስትመንት ግሩፕ ስር ካሉት ተቋማት አንዱ ነው።)

የኮሌጁ ፕሬዚዳንት ናሽናል አቪዬሽን ኮሌጅ ከምስረታው ማግስት ጀምሮ፣ ኢትዮጵያ የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል የምታደርገውን ጥረት ከግብ ለማድረስ በትጋት እየሰራ እንደሚገኝ የገለፁ ሲሆን፣ በዚሁ መሠረትም የሚሰጣቸው የትምህርት ዘርፎች ሀገራችን ለምታካሄደው ሁለ-ገብ ልማት ጉልህ አስተዋጽኦ ያላቸው በርካታ ምሁራንን ማፍራቱንም ተናግረዋል።

ከዚህ ውስጥ ሰፊውን የተሳትፎ ደረጃ የያዙትን ሴቶች ጨምሮ፤ ምሩቃኖቹ በሥራቸው ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ በመሆን ላፈራቸው፣ ለናሽናል አቪዬሽን ኮሌጅም ሆነ ለሀገራቸው መልካም አምባሳደር ሆነው በመሥራት ላይ ይገኛሉ።

በጽሑፍ በተነበበው መልእክት ላይ እንደሰፈረው፣ በኮሌጁ ለትምህርት ጥራት የሚሰጠው ትኩረት ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ በየጊዜውም የትምህርት ጥራት ማሻሻያ መርሃ ግብሮችን ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል፤ የዘንድሮው የ10ኛው ዙር ምሩቃንም የዚሁ ውጤቶች ማሳያ ናቸው።

ኮሌጁ በዘንድሮ የከፍተኛ ትምህርት የመውጫ ፈተና (Exit Exam) ካስፈተናቸው ተማሪዎች ውስጥ 64 በመቶ የሆኑትን ማሳለፉ ኮሌጁ በትምህርት ጥራት ላይ ከፍተኛ ሥራዎችን በመሥራት ላይ እንደሆነ አንድ ጥሩ ማሳያ ነው ተብሏል፡፡

**‹‹የኮሌጁ ፕሬዚዳንት ናሽናል አቪዬሽን ኮሌጅ ከምስረታው ማግስት ጀምሮ፣ ኢትዮጵያ የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል የምታደርገውን ጥረት ከግብ ለማድረስ በትጋት እየሰራ እንደሚገኝ የገለፁ ሲሆን፣ በዚሁ መሠረትም የሚሰጣቸው የትምህርት ዘርፎች ሀገራችን ለምታካሄደው ሁለ-ገብ ልማት ጉልህ አስተዋጽኦ ያላቸው በርካታ ምሁራንን ማፍራቱንም ተናግረዋል።››**

በአጠቃላይ ኮሌጁ ከኢፌዴሪ ትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን ባገኘው እውቅና መሠረት በሁለተኛ ዲግሪ Aviation Management, Hospitality Management, Logistics and Supply Chain Management, Business Leadership, Strategic Management, Banking and Finance, Risk and Insurance, International Trade and Economics, እንዲሁም በመጀመሪያ ዲግሪ በመደበኛ Aviation, Hotel Management, Marketing Management, Accounting and Finance በTVT የተለያዩ ዘርፎች በሆቴልና ቱሪዝም፣ በበረራ መስተንግዶ፣ በጤና በመደበኛ መርሃ ግብር የሚያስለጥን ሲሆን፤ በርቀት መርሃ ግብር ደግሞ Economics, Business Management, Accounting and Finance, Educational Planning Management, Rural Development ፕሮግራሞች ሥልጠና በመስጠት በየዓመቱ በማስመረቅ ላይ ይገኛል።

በተለያዩ የማህበራዊ አገልግሎት ዘርፎች ጉልህ ተሳትፎ እያደረገ የሚገኘው ናሽናል አቪዬሽን ኮሌጅ በሀገሪቱ ውስጥ ካሉ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በተለየ "International Air Transport Association (IATA) & International Commercial Management (SM) በአገኘው እውቅና መሠረት በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያላቸውን ስልጠናዎች እየሰጠ የሚገኝ ሲሆን፣ በሚሰጠው የስልጠና ጥራትም ከAA እና CM የ2016፣ የ2017 እና የ2018፤ ለሶስት ተከታታይ ዓመታት "Africa Top Performing IAIA Authorized Training Center" የሚል ሽልማት ማግኘቱ ተገልጿል፡፡

በዚህ የምረቃ ሥነ ሥርዓት ላይ የተመራቂ ወላጆች፣ የኮሌጁ ማህበረሰብ አባላት፣ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች፣ እንዲሁም ከጎረቤት ሀገር ኬንያ እውቅ ዩኒቨርሲቲዎች የመጡ ተጋባዥ ፕሮፌሰሮች ተገኝተዋል፡፡ በምረቃ በዓሉ ላይ አዲስ ዘመን ተገኝቶ ያነጋገራቸው ምሩቃንም ኮሌጁ በጥሩ ሁኔታ አሰልጥኖ ለምረቃ እንዳበቃቸው ገልጸዋል፡፡

ከነዚህ ተመራቂዎች ውስጥ አንዷ የስድስት ወር ኮርሷን በማጠናቀቅ በቲኬቲንግ የተመረቀችው አትጠገብ የወንድወሰን ናት፡፡ እርሷ እንደምትለው በተቋሙ የነበራት ቆይታ ደስ የሚል ነበር፡፡ በኮሌጁ ታታሪ መምህራኖች አማካኝነት በሰለጠነችበት ሙያ ጥሩ እውቀት ይዛ ወጥታለች። ይህንን እውቀቷንም ወደ ሥራ የመቀየር ፍላጎቷ ከፍተኛ ነው። ለሥራም ዝግጁ ነች። በመሆኑም ወደ ሥራ ዓለም በመሰማራት የእለቱ ደስታዋ ዘላቂ እንዲሆን ትመኛለች፡፡ በሌሎች የጥናት መስኮችም ትምህርቷን የመቀጠል ፍላጎት አላት። ለዚህ ያበቋትን ቤተሰቦቿንም ታመሰግናለች።

ሌላው በኮሌጁ የInternational Trade and Economics ክፍለ ትምህርት ተመራቂ የሆነው ሙሉቀን ደስታው በመመረቁ እጅግ ደስተኛ መሆኑን ተናግሯል። እርሱ እንደሚለው ይህንን የሁለት ዓመት ጊዜ የሚጠይቀውን የጥናት መስክ የተከታተለውና የሁለተኛ ዲግሪ (ኤምኤ) ባለቤት ሊሆን የቻለው በምርጫውና ፈልጎት በመማር ነው። "ትምህርቱ አዋጭ ስለሆነ ሥራ የመሥራት እቅዴ በግል ነው። ስለዚህ ተቀጥሬ መሥራት አልፈልግም" ሲል ተናግሯል፡፡

ለወጣቶች ምክሩን ሲያስተላልፍም "ወጣቶች ወደ ትምህርት ዓለም (ዩኒቨርሲቲ) ሲመጡ ማዳመጥ ያለባቸው ራሳቸውን ነው፡፡ የሚፈልጉትንና የሚችሉትን ማጥናት ይኖርባቸዋል። በቤተሰብ ወይም በሌላ ሰው ግፊት መሆን የለበትም። እራሳቸውን አዳምጠው፣ ፍላጎታቸውን አውቀው ከሆነ ነው ውጤታማ መሆን የሚችሉት" በማለት ሃሳቡን አካፍሏል። መመረቁን ተከትሎም ከሚገባው በላይ ቤተሰቦቹ መደሰታቸውን፤ ጓደኞቹም በእሱ መመረቅ የተሰማቸውን ደስታ እየገለፁለት እንደሆነ ተናግሯል፡፡

ናሽናል አቪዬሽን ኮሌጅ በግስጋሴ ላይ ነኝ እያለ ነው፡፡ ግስጋሴው ታዲያ ያለ ምንም መደነቃቀፍና እንከን እንዲሆን፤ ሀገርና ወገንንም የሚያገለግል፣ ስምንም የሚያስጠራ ተቋም እንዲሆን የሁሉም ሀገር ወዳድ ህብረተሰብ ምኞት ነው፡፡

# ‹‹አፋር የኢትዮጵያ የብልፅግና ምልክት እንዲሆን በጋራ እንሠራለን››

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

ምሕረት ሞገስ



የሰው ዘር መገኛ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ዳሎል እና ኤርታሌን በመያዙ ተለይቶ የሚታወቀው ሞቃታማው የአፋር ክልል በወረሃ ጥቅምት መግቢያ፤ የሀገሪቱን መሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን (ዶ/ር) ለመቀበል ሽርጉድ ሲሉ ከራርሟል፡፡ ጥቅምትን አጋምሰው በቀን 17 የሠመራ ሱልጣን አሊሚራህ ሃንፈሬ አየር ማረፊያን የረገጡት ጠቅላይ ሚኒስትር፤ በክልሉ ሕዝብ የሞቀ አቀባበል ተደርጎላቸዋል፡፡

በአቀባበሉ የአፋር ወጣት ወንዶች የፀጉራቸው ውበት የሚያስደንቅ ሲሆን፤ ነጭ ባህላዊ ልብሳቸው እና ጭፈራቸውን አስተውሎ ለተመለከተው በልብ ውስጥ የተለየ የደስታ ስሜትን ይፈጥራል፡፡ ወጣት ሴቶችም በቀይ እና ቢጫ ሻርፐ ፀጉራቸውን ሸፋፍነው ከወገባቸው በታች አብረቅራቂ ቀሚስ አጥልቀው በእልልታ የታጀበ ባህላዊ ጭፈራ ሲያቀርቡ፤ እጅግ የሚያዝናና ነበር፡፡

የሠመራ አየር ማረፊያ ተገኝተው ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የሞቀ አቀባበል ያደረጉት፣ ወጣቶች እና የክልሉ ባለሥልጣናት ብቻ ሳይሆኑ፤ ታዋቂ የሀገር ሽማግሌዎችም ተገኝተው ነበር። የክልሉ ወጣቶች ባህላዊ ዘፈኑን አቅርበው ሲያጠናቅቁ፤ የአፋር ክልል የፖሊስ ማርሽ ባንድም ሙዚቃዎችን አቅርቧል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ‹‹እንኳን ደህና መጡ›› በሚል የቀረበላቸውን አበባ ተቀብለው፤ በቅርብ ለተገኙት ለክልሉ ባለሥልጣናት እና ለታዋቂ የሀገር ሽማግሌዎች ሰላምታ ሰጥተው፤ ከአየር ማረፊያው ሲወጡ የክልሉን የባህል ዘፈን በማቅረብ በፈገግታ ከሸኟቸው ወጣቶች ሌላ፤ በአካባቢው ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ አቀባበል አድርጎላቸዋል፡፡

ራሳቸው መኪና እያሽከረከሩ፤ ርዕሰ መስተዳድሩ አቶ አወል አርባ እና ሌሎች ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ከአየር መንገድ ወደ መሃል ከተማዋ ሲገቡ የሕዝቡ አቀባበል የተለየ ነበር፡፡ በግራ እና በቀኝ የተደረደረው የከተማዋ ሕዝብ እያጨበጨበ በእልልታ ደስታውን ገልጿል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከተማውን አልፈው በቀጥታ ያመሩት ወደ ክልሉ የእርሻ ልማት ነበር፡፡ ፓፓያ እና ሌሎችም ፍራፍሬዎች ወደ ተተከሉባቸው እና ምርት ወደ ተሰበሰበበት አካባቢ የተጓዙ ሲሆን፤ ከተሰበሰበው ምርት በተጨማሪ በአምስት ወር ውስጥ ተተክለው ፅድቀው ለማበብ የደረሱ የፓፓያ ተክሎችንም ጎብኝተዋል፡፡ በክልሉ ያለውን የመሬት፣ የውሃ እና የሰው ሀብትን በመጠቀም አፋር ወደ ከፍተኛ አምራችነት እንዲሸጋገር ማድረግን በማሰብ የበጋ ስንዴ በይፋ የተጀመረው በዛው ክልል ነበር፡፡

## የበጋ ስንዴ

ለስንዴ እርሻ በማሽኖች እየተዘጋጀ ያለውን መሬት ካዩ በኋላ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ንግግር አድርገዋል፡፡ ኢትዮጵያ እጅግ የማደግ አቅም ያላት ሃብታም ሀገር መሆኗን አስታውሰው፤ የአፋር ክልል ኢትዮጵያ ሊታረስ የሚችል መሬት፤ ያልወጣ እና ወደ ገንዘብ ያልተቀየረ ማዕድን፤ ሰፊ ጉልበት እና መማር እንዲሁም መሥራት የሚችል የሰው ኃይል አላት ለሚለው ማሳያ መሆን እንደሚችል አብራርተዋል፡፡

የአፋር ክልል እሾህ ውስጥ እንዳለ እንደ ክዋኖ ፍሬ ነው፡፡ የክዋኖ ፍሬ በእሾህ ውስጥ ያለ ፍሬ ስለሆነ፤ አግኝቶ ፈልቅቆ ለመጠቀም ያስቸግራል። ነገር ግን አንዴ እሾሁን ተጠንቅቀው ፍሬውን ካወጡ ምግብ ብቻ ሳይሆን መድኃኒትም ማግኘት ይቻላል፡፡ የክዋኖ ፍሬ ለብዙ ነገር ይጠቅማል፤ ያንን እሾህ ውስጥ ያለ ፍሬ ፈልቅቆ ለማውጣት ጥንቃቄ እንደሚያስፈልገው ሁሉ በአፋር ምድርም እርሻን፣ ማዕድንም ሆነ ኢንደስትሪ ሲታሰብ መልከዓ ምድሩ በቀላሉ የሚታሰበውን ጣፋጭ ፍሬ ለመቅመስ የሚያስችል አይደለም፡፡ ጥረት እና ሥራ ይፈልጋል ብለዋል፡፡

> **መንግሥት እርሻ ላይ ጣልቃ መግባቱ እና የአፋርን መሬት ሰንጥቆ ከአዋሽ ጋር አገናኝቶ እንዲታረስ ማድረጉ ብቻ ሳይሆን ማዳበሪያ ከመንግሥት አግኝቶ የማያውቅ ክልልን ማዳበሪያ ከመንግሥት እንዲያገኝ ማስቻሉ በራሱ በጣም ትልቅ ድል ነው**

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለስንዴ እርሻ እየተዘጋጀ ያለውን የእርሻ መሬት ሲጎበኙ ባደረጉት ንግግር፤ ‹‹እንደ ሀገር የበጋ ስንዴ ዝንባሌ በጣም የሚገርም ነው፡፡ የድሮ ተትቶ የአምና እና የዘንድሮ በሀገር ደረጃ ሲወዳደር፤ የዘንድሮ ሶስት ሚሊየን ሄክታር ነበር፤ ከአምናው በ1 ነጥብ 7 ሚሊየን ሄክታር ይበልጣል። ይህ ከእጥፍ በላይ ነው፡፡ በምርትም ደረጃ አምና የሰበሰብነው በጋ ላይ 47 ሚሊየን ኩንታል ገደማ ነበር፡፡ ዘንድሮ ደግሞ በበጋ ብቻ 100 ሚሊየን ኩንታል ይጠበቃል፡፡ የበጋ እና የክረምት ምርታችን ከስድስት ሚሊየን ሄክታር በላይ አልፏል። ይህ በጣም ተጨባጭ ትልቅ እድገት ነው፡፡›› ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ዘንድሮ ዝናቡ እና የክረምት እርሻው ጥሩ እንደነበር አስታውሰው፤ በስፋት ሁለት ሚሊየን ሄክታር የተጨመረ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ምርቱ በጣም ጥሩ መሆኑን እና አሁን በአብዛኛው እየተሰበሰበ እንደሚገኝም ነው የገለፁት፡፡ አሁንም በእዚህ መቆም አይገባም፤ በአግባቡ መቀጠል ያስፈልጋል፡፡ የክረምቱ ተሳክቶ ሲጠናቀቅ ቶሎ የበጋ ስንዴ ካልተጀመረ እና በክረምት ስንዴ ተዝናንቶ ወደኋላ ማለት ወይም ማቆም ከመጣ ውጤቱ ቀጣይነት እንደማይኖረው አመላክተዋል።

ሶስት ሚሊየን ሄክታር ማልማት በጣም ሰፊ ነው፤ ይህ ቢሆንም በሀገር ደረጃ ሲደማመር የታሰበውን ማግኘት ይቻላል፡፡ አፋር እና ሌሎችም ክልሎች ላይ በጣም ምርጥ አፈር አለ፤ ውሃ አለ፡፡ ይህን አቀናጅቶ በመጀመር ወደ ውጭ መላክ ብቻ ሳይሆን ለብዙ ነገር ማዋል ይችላል፡፡ ምክንያቱም አሁን የሚመረተው ድሮ ከሚመረተው በጣም በብዙ እጥፍ የበለጠ ነው። ይህን ለማድረግ ሁሉም ቦታ ላይ ያለውን ሀብት ማየት፣ ፈልቅቆ ማውጣት እና መጠቀም ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳብራሩት፤ አሁን ስላለው ለውጥ ብዙ በትክክል የማይገነዘብ ሰው አለ፡፡ ለብዙ ጊዜ አጋር ተብለው የተከለሉት አፋር፣ ጋምቤላ፣ ቤንሻንጉል እና ሶማሌ የተገለሉት በፖለቲካ ብቻ አልነበረም። ማዳበሪያም አይሰጣቸውም ነበር፡፡ የተገለሉት ፖለቲከኞቹ ብቻ ሳይሆኑ አርሶ አደሮቹም የተከለሉ ነበሩ። ማዳበሪያ የሚሰጣቸው ትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ እና ደቡብ ክልሎች እንጂ ሌሎቹ አያገኙም ነበር፡፡ መንግሥት ማዳበሪያ የተወሰነ በሚሊየን የሚቆጠር ድጎማ ይሰጥ ነበር። ድጎማው የሚሄደው ለኢህአዴግ ክልሎች እንጂ እነቤንሻንጉል፣ አፋር፣ ጋምቤላ እና ሶማሌ ጭራሽ ተቋምም ሆነ ሥርዓት የላቸውም ነበር፡፡

‹‹ማዳበሪያን በተመለከተ አምና ቤንሻንጉል ጀምረናል፤ ዘንድሮ አፋር ጀምረናል፤ አሁን ሶማሌ ላይ እየሰራን ነው፡፡ ቀጥሎ ሶማሌን ካስገባን በፖለቲካው ብቻ ሳይሆን በማዳበሪያውም አርሶ አደሩ የመጠቀም፣ ትራክተር የመግዛት፣ መሬቱን የማልማት ሁኔታው እያደገ ሲሄድ እንደ ሀገር እናድጋለን፡፡ እድገቱ፣ ቱሪዝሙ፣ ኢንዱስትሪው ሁሉም ጋር ይሁን ሲባል አንዱ ማሳያ ይሄ ነው።›› ብለዋል፡፡

መንግሥት እርሻ ላይ ጣልቃ መግባቱ እና የአፋርን መሬት ሰንጥቆ ከአዋሽ ጋር አገናኝቶ እንዲታረስ ማድረጉ ብቻ ሳይሆን ማዳበሪያ ከመንግሥት አግኝቶ የማያውቅ ክልልን ማዳበሪያ ከመንግሥት እንዲያገኝ ማስቻሉ በራሱ በጣም ትልቅ ድል ነው፡፡ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በሌላ በኩል ከአፋር የሚሰበሰበውን ስንዴ ሁሉም ይመገበዋል። ምርቱ ወደ ውጭ ከተላከም ሁሉም ይጠቀማል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

‹‹አፋር ሲሰራም ብርቱ ነው፤ ሲዋጋም ብርቱ ነው፡፡ አሁን አይቶ ማረጋገጥ እንደሚቻለው እርሻውም ልዩ ነው፡፡ አፋር በጣም ሃብታም ክልል ነው፡፡ መላው ኢትዮጵያውያን ከአፋር ወንድሞቻችን ጋር በመተባበር ክልሉን ማልማት እና ለሌሎችም እንዲጠቅም ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ ይሄ ዛሬ ላይ የታረሰው መሬት አብቅሎ ለመብላት

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# ‹‹አፋር የኢትዮጵያ የብልፅግና...

ከ ገጽ 9 የዞረ

ያበቃናል።›› ብለው ተስፋቸውን በመግለፅ የበጋ ስንዴ በይፋ አስጀምረዋል፡፡

በድጋሚ ሶስት ሚሊየን ሄክታር መሬት ዘንድሮ እንደሚታረስ እና ከአምናው በእጥፍ የሚበልጥ መሆኑን በማስታወስ፤ በየክልሉ ሁሉም ትኩረት ሰጥቶ በትጋት መሥራት ይኖርበታል ሲሉ ማሳሰቢያ ሰጥተዋል፡፡ ከምግብ ልመና ነፃ የወጣች ኢትዮጵያን ዕውን ማድረግ የሚቻለው፤ ይህ ሲሳካ ብቻ ነው ብለዋል፡፡

ክረምት ላይ መሠራቱ ጥሩ ነገር ነው፡፡ እርሱ መሰብሰብ አለበት፡፡ ነገር ግን ክረምት ቢሠራም በጋም ላይ መሠራት አለበት፡፡ ልክ በጋ ላይ ሲጨረስ ደግሞ ክረምት ይቀጥላል፡፡ ሌማትም ሆነ አረንጓዴ ልማት በተመሳሳይ መልኩ ማስቀጠል የግድ ነው፤ ይሄ ሲደማመር የኢትዮጵያን ብልፅግና ያለምንም ጥርጥር መጨበጥ ይቻላል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

### ገበታ ለትውልድ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) አፋር ክልል ሄደው የበጋ ስንዴን ከማስጀመር እና የእርሻ መሬት ከመጎብኘት በተጨማሪ ገበታ ለትውልድ የሚል ፕሮጀክት የሚሠራበትን ቦታም አይተዋል። ከዚህ በፊት ከተመረጡት ቦታዎች በሙሉ ሻል ያለ መሆኑን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ አርባ ምንጭ በጣም ጥሩ ቦታ ተመርጧል፡፡ በጅማ እና በምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሚዛን አካባቢም በጣም ጥሩ ቦታ ተመርጧል፤ በአፋርም ክልል እንደዚሁ የፓልም እርሻ ያለበት እጅግ በጣም ውብ የሆነ ቦታ ተመርጧል። በወሎም የሐይቅ አካባቢ ተመርጧል፡፡ በትግራይ ገራአልታ ተመርጧል፤ በሶማሌ ጅጅጋ አካባቢ ተመርጧል። አብዛኞቹ ቦታዎች እጅግ በጣም ሳቢ ናቸው ብለዋል፡፡

‹‹ቦታዎቹ ለቱሪስት ውብ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን እኛንም እንዲህ ዓይነት ቦታ አለን ወይ? ብለን እንድንጠይቅ የሚያደርገን ነው፡፡›› ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ይህ በአፋር ክልል የሚገኘው ቦታ ከአዋሽ ጅቡቲ የሚሠራው ከአዲሱ የፍጥነት መንገድ በ25 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ነው ብለዋል፡፡ ልክ ከፍጥነት መንገዱ ሲወጣ አሁን የተመረጠው ቦታ ከሁለት ፓርኮች ማለትም በአሰቦት እና በአዋሽ ፓርክ መካከል የሚገኝ ቦታ መሆኑን አሳውቀዋል፡፡

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለፃ፤ ቦታው በጣም ብዙ አዕዋፋት፣ የዱር እንስሳት እና ሰፋፊ እርሻዎች የሚገኙበት ነው፡፡ በየትኛውም ዓለም ፓልም እጅግ በብዛት እንደ ማንኛውም ዛፍ ጫካ ሆኖ የሚታይበት አካባቢ አያጋጥምም፤ ይህ ቦታ ግን ፓልም እንደ ጫካ በብዛት የሚገኝበት ቦታ ነው፡፡ ሣሩ የሚገርም ሲሆን፤ ፍል ውሃም አለ፡፡

‹‹በአፋር የተመረጠው ቦታ ሲታይ አሁን ባለበት ሁኔታ እንኳ እኛ ኢትዮጵያውያን ድህነትን ፈልገን፣ መርጠን፣ ተግተን እና ሠርተን ያመጣነው እንደሆነ አንዱ ማሳያ ነው። እንዲህ የሚታረስ ሰፊ ቦታ ኖሮን፤ ንፁህ ውሃ እና ፍል ውሃ ኖሮን፤ እንዲህ ዓይነት ውብ ቦታ ይዞ ‹ተርቤያለሁ እና ምግብ ስጡኝ› ብሎ መለመን ለድህነት ባለ ፍቅር እና ቅርበት በትጋት ተሠርቶ የመጣ ካልሆነ በስተቀር፤ ሰው በረሃን የማይመች ስፍራን ለአራት እና ለአምስት ወራት በበረዶ የተሸፈኑ ቦታዎችን ቀይሮ ራሱን እያበላ እኛ እንዴት ተቸገርን የሚል ጥያቄን ደጋግመን እንድናነሳ ያደርጋል፡፡

ለመገዳደል ብርቱዎች ነን፡፡ ለመተኛት እና ለመተማማት ብርቱዎች ነን፡፡ ለውጊያ አንደክምም። ያለንን የተፈጥሮ ሀብት እና ፀጋ ፈልቅቆ ለማየት እንደክማለን፡፡ እንዲህ ዓይነት ድንቃድንቅ ቦታዎችን ፈልገን አግኝተን ትንንሽ ነገሮችን ጨምረን ለኛ ብቻ ሳይሆን ለዓለም ሳቢ ለማድረግ ደግሞ እንደክማለን። ይሄ ለድህነት



ያለንን ቅርበት እና ምርጫ የሚያሳይ ነው፡፡ ቆም ብለን ካስተዋልን ኢትዮጵያውያን ለመበልጸግ ሁሉ ነገር የተሰጠን ነን፡፡ ›› ብለዋል፡፡

አፋርን ብቻ መመልከት ይቻላል፡፡ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ አፋር እንደሚታወቀው በጣም ሞቃታማ እና በርሃማ አካባቢ ነው፡፡ ነገር ግን አፋር ከባህር ጠለል በታች በጣም ዝቅተኛ ቦታ አለው። በሌላ በኩል እነዳሎል እና ኤርታሌን የመሳሰሉ ሊጎበኙ የሚችሉ መስዕቦች አሉት። ክልሉ የሉሲ መገኛ ብቻ ሳይሆን የተደረጉት በርካታ ጥናቶች እንዳረጋገጡት፤ ከአዋሽ ጀምሮ እስከ አፋር ባለው ቀጠና ውስጥ ኢትዮጵያ የሰው ልጅ መገኛ መሆናችንን ያሳየ መሆኑን አስታውሰዋል፡፡

‹‹በአፋር ታሪክ አለ፤ ለተፈጥሮ የሚሆኑ ቦታዎች አሉ፡፡ የሚገርም የእርሻ ሥራን ማከናወን ይቻላል። አፋር ከሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች በተለየ ሁኔታ አዋሽን የሚያክል ሰጥቶ እና አጠጥቶ የማይጠግብ፤ አረካለሁ ብሎ የማያስብ፤ አልፈልግም ሲባል ርቆ የማይሔድ እና ራሱን እዛው ደብቆ የሚቀር ውሃ ያለው የለም፡፡ አዋሽ አፋርን ገልብጦ ሊያለማ ይችላል፡፡ የስንዴ እርሻን አየን፤ በአምስት ወር ውስጥ የደረሰ የሙዝ እርሻ በአፋር ምድር ላይ እንዴት ሊስፋፋ እንደሚችል አየን፤ ሐምሌ የተተከለ ሙዝ ከአዋሽ አጠገብ በመሆኑ እንዴት እንዳደገ አይተን አረጋገጥን፡፡

ከእርሻ ሲወጣ ደግሞ ማዕድን እንደ ግብዓት የሚጠቀመውን ኢንደስትሪ አየን፡፡ ይህ በሀገር ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የሚፈለግ የኢንደስትሪ ውጤት ነው። ከሀገር ውጭም ከፍተኛ ገበያ ያለው ነው። የመንን ጨምሮ ሌሎችም ሀገሮች ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው አሳውቀዋል፡፡ ነገር ግን ያ ብቻ አይደለም፤ አፋር በጣም በርካታ የማዕድን ውጤቶች ያሉበት አካባቢ ነው፡፡ ከዛ በተጨማሪ ከቱሪዝም አንፃር የታዩ አስደማሚ ቦታዎች አሉ፡፡

በአፋር ቱሪዝም፣ ማዕድን፣ ግብርና እና ኢንደስትሪ በዚህ ዘመን በመንግሥት ውስጥ ካሉ ዋና ዋና የትኩረት ዘርፎች መካከል አራቱን በአፋር ክልል ውስጥ ማከናወን ይቻላል፡፡ አምስተኛው የመንግሥት የትኩረት አቅጣጫ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ(አይ ሲ ቲ) ነው፡፡ እርሱ ደግሞ የማይገባበት ቦታ የለም። ለቱሪዝሙም፣ ለማዕድኑም፣ ለግብርናውም፣ ለኢንደስትሪውም በእጅጉ የሚያስፈልግ ነው፡፡ በመረጥናቸው ዘርፎች ሁሉ ውስጥ በዚህ አካባቢ የጀመርናቸው ሥራዎች ውጤት እንደሚያመጡ የሚያመላክት ነው፡፡›› ብለዋል፡፡

እንደጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለፃ፤ አሁን ወረሃ ጥቅምት ነው፡፡ የአፋር ገበታ ለትውልድ ዓይን ገላጭ ነው፡፡ ከሁለት ዓመት በኋላ በአሰቦት እና በአዋሽ ፓርክ መካከል የሚገኘው

> ‹‹ በአፋር የተመረጠው ቦታ ሲታይ አሁን ባለበት ሁኔታ እንኳ እኛ ኢትዮጵያውያን ድህነትን ፈልገን፣ መርጠን፣ ተግተን እና ሠርተን ያመጣነው እንደሆነ አንዱ ማሳያ ነው

ለቱሪዝም የታሰበው ቦታ ላይ ማደር ይቻላል፡፡ ‹‹የምንጀምረው ዝም ብለን አይደለም፤ ያለምንም ጥርጥር ተቆጣጥረን፣ ሠርተን፤ አሠርተን እና ተከታትለን እናስፈፅመዋለን፡፡ ጨርሰን ሰዎች የሚገለገሉበት ይሆናል፡፡ ንፁህ ህሊና ያላቸው ኢትዮጵያውያን ከሁለት ዓመት በኋላ፤ ቦታውን ሲያዩ ‹ እንዴት ከድህነት ጋር ተዋደን ተጋብተን ተስማምተን ኖርን? ምን ነክቶን ነበር?› የሚል ጥያቄ ማንሳታቸው አይቀርም፡፡ ማንኛውም ጤነኛ ሰው እንደዚህ ዓይነት ስጦታ እና መልካም ነገርን ይዘን መራባችንን ሊቀበል አይችልም፡፡›› ብለዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ አፋር ላለፉት 30 ዓመታት አጋር የሚል ስያሜ ይዞ በክልልነት ሲቆይ ለመጀመሪያ ጊዜ ማዳበሪያ በመንግሥት ያገኘው ዘንድሮ ነው። እስከ ዛሬ ልክ እንደ ፖለቲካው ሁሉ ማዳበሪያም ተከልክሎ እንደዚሁ ክልል እና አጋር ተብሎ ቀርቶ ነበር፡፡ አሁን ግን ማዳበሪያ እና እርሻ ብቻ ሳይሆን በቱሪዝምም ሌሎች ክልሎች ያገኙትን እንዲያገኝ ተደርጓል ሲሉ ይህ ትልቅ ትርጉም ያለው መሆኑን ደጋግመው አመልክተዋል፡፡

በፍራፍሬ አስደናቂ ነገር ታይቷል፡፡ በማዕድን በጣም በርካታ ፋብሪካዎች እየተጀመሩ ነው። እነዚህን አሰናስኖ፤ ተግቶ እና ሰርቶ ኢትዮጵያን ወደ ብልጽግና የሚወስደውን መንገድ በተሟላ መንገድ እንዲሆን የማረጋገጥ ሥራ ይጠበቃል፡፡ ለመሰዳደብ፣ ለመጠላላት እና ለመገዳደል ብርታት ካለ ለሌላው ነገር የሚውለውን ጉልበት ቀንሶ፤ በልማት እና በሥራ ላይ ቢውል ምን ሊመጣ እንደሚችል መገመት ይቻላል ብለዋል፡፡

‹‹ሁልጊዜ እንደምንደነቀው፤ በአፋር በአሰቦት እና በአዋሽ ፓርክ መካከል የሚገኘው ለቱሪዝም የታሰበው ቦታ ሲታይ፤ መላው ኢትዮጵያ ሲቃኝ እንዴት ፈጣሪ አዳልቶ እንደሰጠን እና ሁሉ ነገር ያላት ሀገር መሆኗን እንደምናየው ሁሉ በአፋርም ያለው አስደማሚ መሆኑን በዓይናችን አረጋግጠናል። ሰው የአፋር ክልል ለም ነው ብሎ ላያስብ ይቻላል፤ አይተን እንዳረጋገጥነው ፍልውሃ በአንድ አካባቢ 20 እና 30 ሐይቆችን ሠርቷል፡፡ የሚያስደንቅ እርሻ አለ፡፡ ሪዞርቱ እርሻንም ያካተተ ነው፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የብዙ ሰዎች መዝናኛ፣ ማረፊያ፣ ማሰቢያ እና የብዙ ሰዎች የማይረሳ ትዝታ የማሳለፊያ ቦታ ይሆናል፡፡

ከአዲስ አበባ በፈጣን መንገድ በሁለት ሰዓት ውስጥ ሳፋሪ አዋሽን እና ሰቦትን አይቶ ፀዳ ያለ ሪዞርት ላይ አርፎ መሔድ አስደሳች ይሆናል። ከመሃል ከተማ ያለው ርቀትም በየትኛውም መስፈርት ከዓለም ተመራጭ ቦታ ያደርገዋል። ይህንን ለማሳካት በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ በትጋት ሠርተን ይህንን ቦታ ውብ አድርገን መልሰን ውጤት እናሳያለን፡፡ ›› ብለዋል፡፡

‹‹ላለፈው አንድ ዓመት አካባቢ ብዙ ስንመላለስ ነበር፡፡ መንገድ አልነበረም፡፡ መምጣት ከባድ ነበር። የደከምንባቸው እና የወደቅንባቸው ጊዜዎች ነበሩ።›› ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ አሁን የተሻለ መንገድ እና የሂሊኮፍተር ማረፊያ አለ፡፡ ከዚህ በኋላ የበለጠ የተሻለ ይሆናል፡፡ በእኛ በኢትዮጵያውያን የተደመረ ትጋት፤ በቁርጠኝነት በምንሠራው ሥራ እጅግ ያማረ ነገር እንደምናይ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡›› ሲሉ ምኞታቸውን ገልጸዋል፡፡

‹‹ለአፋር ሕዝብ እንኳን ደስ አላችሁ በቅርብ ድንቅ የሆነ የፈጣሪ ስጦታ አላችሁ፡፡ ከአፋር ብርቱ ሕዝብ ጋር ተጋግዘን አፋርን በመቀየር አፋር ለኢትዮጵያ የብልፅግና ምልክት እንዲሆን በጋራ እንሠራለን። አፋርን ስንለውጥ፤ ሶማሌን ስንለውጥ፤ ጋምቤላን እና ቤንሻጉልን ስንቀይር፤ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያን ስንቀይር ኢትዮጵያ ትቀየራለች።›› ካሉ በኋላ፤ ለዚህ ግብዓት መሆን የሚችል ሥራ ተጀምሯል፤ ከሁለት ዓመት በኋላ በውጤት እንገናኛለን ሲሉ መልዕክታቸውን አጠቃለዋል፡፡

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ቆዳና ጸጉር ለመንከባከብ የሚያገለግሉ ተኪ ምርቶች

**ወርቅነሽ ደምሰው**

በሀገራችን ቆዳንና ጸጉርን ለመንከባከብ የሚያገለግሉ የተለያዩ የምርት ዓይነቶች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ ከእነዚህ ምርቶች አብዛኞቹ በፋብሪካ የተቀነባበሩና ከውጭ ሀገር የሚገቡ ናቸው። ተጠቃሚዎችም እነዚህን ምርቶች ከገበያ ላይ ገዝተው ይጠቀማሉ፡፡ ለዚህም ዋነኛው ምክንያት በሀገር ውስጥ የሚመረት አማራጭ የመዋቢያ ምርት እምብዛም አለመኖሩ ነው፡፡

ይሁንና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተፈጥሯዊ (ኦርጋኒክ) ምርቶችን በሀገር ውስጥ የሚያመርቱ ድርጅቶች ብቅ እያሉ ስለመሆናቸው ገበያዎችና አንዳንድ መድረኮች እየጠቆሙ ናቸው፡፡ ከእነዚህም መካከል ለቆዳና ለጸጉር እንክብካቤ የሚያገለግሉ ምርቶችን በሀገር ውስጥ እያመረተ የሚገኘው «ጥላ» የተሰኘው ድርጅት አንዱ ነው፡፡

ድርጅቱን ያገኘነው በአፍሪካ የፋሽን ሳምንት ዝግጅት ላይ ነው፡፡ ወደዚህ ሥራ ከገባ ሦስት ዓመታት ያህል አስቆጥሯል፡፡ የድርጅቱ ምርቶች 96 በመቶ ያህሉ ተፈጥሯዊ (ኦርጋኒ) ከሆኑ ነገሮች የሚመረቱ መሆናቸውን የጥላ ብራንድ አምባሳደር ወጣት ዓለምፀሐይ ቤዛው ትናገራለች፡፡

ብራንድ አምባሳደሯ እንደምትለው፤ እነዚህ ምርቶች በሀገር ውስጥ ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲዘጋጁ ይደረጋል፤ ምርቶቹም ለሀገር ውስጥ ገበያ ይቀርባሉ፤ ለውጭ ገበያም ይላካሉ፡፡

ድርጅቱ ብራንድ የሆኑ ተፈላጊ ምርቶችን ያመርታል፡፡ እስካሁን ድረስ ለቆዳና ለጸጉር ተብለው በሀገር ውስጥ የተሰሩ መዋቢያና መንከባከቢያ ምርቶች የተለመዱ አይደሉም ያለችው ወጣት ዓለምፀሐይ፣ ለዚህም ከውጭ ሀገር የሚመጡ ምርቶችን ለመጠቀም እንገደዳለን ትላለች፡፡ ከውጭ የሚገባው ምርት ደግሞ ነጮቹ ለእነሱ ቆዳ በሚሆን መልኩ የሚያመርቱት መሆኑን ጠቅሳ፣ ይህ ምርት ለኢትዮጵውያን ቆዳና ጸጉር ተስማሚ ላይሆን ይችላል ብላለች፡፡ ድርጅቱ በሀገር ውስጥ የሚያመርታቸው ምርቶች ግን ለኢትዮጵያውያን ብሎም ለአፍሪካውያን ቆዳና ጸጉር እንደሚስማሙም ትገልጻለች፡፡

እሷ እንዳለችው፤ እነዚህን ምርቶች ለማምረት ድርጅቱ የሚጠቀምባቸው ጥሬ እቃዎች ሺያ ቅቤ፣ ካካዎ፣ ቅቤና ጥቁር አዝሙድ ናቸው፡፡ ከእነዚህም ክሬም፣ ሻውር ጄል፣ የጸጉር ሻምፖ፣ የጸጉር ትሪትመንት (መንከባከቢያ) ኮንዲሽነር እና ቦዲ ሎሽን ይመርታሉ። በውስጣቸው ያለው ይዘትም ሺያ ቅቤ ክሬም ቫይታሚን ያለው ነው፡፡ የካካዎ ክሬም ምርት ደግሞ የካካዎ ቅቤና ጥቁር አዝሙድ ያለው ሲሆን፣ ሁለት ዓይነት ሆኖ አንዱ በዘይት አንደኛው ደግሞ በውሃ የሚሰራ ነው፡፡

የሻውር ጄሉ ከንጹህ ነጭ ማር ይመረታል፡፡ የጸጉር ሻምፖ ደግሞ ከአቡካዶ ዘይትና ከግሪስሊን የሚሰራ ሲሆን፣ የጸጉር ትሪትመንቱ (መንከባከቢያ) የአቡካዶ ዘይት ያለው ነው፡፡ ኮኮናት ዘይቱም እንዲሁ ንጹህና መቶ በመቶ የተጣራ ሲሆን፣ ለጸጉር፣ ሰውነት ማሳጅ ለማድረግና ለሁሉም ዓይነት አገልግሎት የሚውል ነው፡፡

ምርቶቹ ከሕጻን እስከ አዋቂ ለሁሉም ሰው ቆዳና ጸጉር ተስማሚ በሆነ መልኩ እንደሚዘጋጁ ብራንድ አምባሳደሯ ጠቁማ፤ ደረቅና ወዛም ለሚባሉ የቆዳ ዓይነቶች እንዲስማሙ ተደርገው የተዘጋጁ መሆናቸውንም ገልጻለች፡፡ ምርቱን ለመግዛት የሚመጡ ሰዎች ለቆዳቸው የሚስማማቸውን ዓይነት ምርት እንዲያገኙ ለማድረግም ይሰራል፡፡ ለዚህም በቅድሚያ የትኛው የቅባት ዓይነት ለቆዳቸው ይስማማል የሚለው ታይቶ በእጃቸው ላይ ሞክረው እንዲያዩ ከተደረገ በኋላ ለቆዳቸው የሚስማማቸውን ዓይነት ምርት እንደገዙ እንደሚደረግ ትናገራለች፡፡

ወጣት ዓለምፀሐይ እንደተናገረችው፤ ምርቶቹን በቅድሚያ በእጅ ላይ እንዲሞከሩ የሚደረግበት ዋንኛ ምክንያት አንዳንድ ሰዎች ለእንደዚህ ዓይነት ምርቶች አለርጂክ ሊሆኑ ስለሚችሉ ነው፡፡ አንድ በእጁ ቆዳ ላይ ሞክሮ አለርጂክ ከሆነበት ወዲያውኑ ይታያል፡፡ ይህም ምርቱን እንዳይጠቀም ለማድረግ ይረዳል፡፡

እነዚህ ምርቶች ተፈጥሯዊ ስለሆኑ በሰዎች ላይ የሚያስከትሉት ምንም ዓይነት የጎንዮሽ ጉዳት የለም፡፡ ለወንድ ወይም ለሴት ተብሎ የሚለዩ ሳይሆን ለሁሉም ሰው የሚሆኑ ምርቶች ናቸው፡፡

ምርቶቹን የተጠቀሙ ደንበኞች የሚሰጡት አስተያየት ለድርጅቱ ሥራ የሚያበረታታ ሆኖ መገኘቱንም ነው ብራንድ አምባሳደሯ ያመለከተችው። «ሰዎች ምርቶቹን ከተጠቀሙ በኋላ በቆዳቸውም ሆነ በጸጉራቸው ላይ ወዲያውኑ ለውጥ እንደሚያዩና ምርቶቹንም በጣም እንደሚወዷቸው ገልጻለች፡፡ አብዛኞቹ ሰዎች ምርታችንን መጠቀም እስኪጀምሩ እንጂ ከጀመሩ በኋላ ወደ ሌላ በፍጽም አይሄዱም። በጣም ስለሚስማማቸው ያልተጠቀሙበትን ጊዜ ይቆጩበታል፡፡» ስትል ታብራራለች፡፡

ብራንድ አምባሳደሯ እንደምትለው፤ ምርቶቹ የሁሉንም ሰው የመግዛትና የመጠቀም አቅምም ያማከሉ ናቸው፡፡ ሰዎች ምርቱን በእጃቸው ቆዳ ላይ ሞክረው በተደጋጋሚ ተቀብተው አይተውትና ወደውት እንዲገዙ ለማድረግ እንዲያስችልም በትንሽ መጠን የሚዘጋጁ ምርቶችም አሉ፡፡

«በኛ የቆዳ ዓይነት ያልተሰሩ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ብዙ ሺ ብሮችን አውጥተን እንገዛለን፤ ይህንን ሁሉ ብር አውጥተን ገዝተንም ብዙም የማንረካበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል» የምትለው ብራንድ አምባሳደሯ፤ ከዚህ አንጻር የጥላ ምርቶች ዋጋቸው ተመጣጣኝ እንደሆኑ ትናገራለች፡፡

«በተለይ እንደዚህ ዓይነት የዓለም አቀፍ የፋሽን ኤግዚቢሽን ላይ ስንቀርብ ደግሞ ሱቅም ከሚሸጥበት ዋጋ በታች ቀንሰን እንሸጣለን፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት መድረኩ ከተለያዩ ሀገሮች የመጡ ሰዎች የሚገኙበት እንደመሆኑ መጠን የገበያ ትስስርን ማስፋት የሚቻልበት አጋጣሚ ስለሚፈጥር ነው ብላለች፡፡ ለምሳሌ በአሁኑ ኤግዚቢሽን የዋጋ መቀነስ ብቻ ሳይሆን ምርቶቻችንን ለሚገዙ (ሁለት ትላልቅ ተመሳሳይ ምርቶች የገዛ ሰው) ሌላ አንድ ምርት በስጦታ የሚያገኙበትን ሁኔታ ፈጥረናል፡፡ ሌሎች ተጨማሪ ስጦታዎችም አሉ» ስትል አብራርታለች።

እሷ እንዳለችው፤ ድርጅቱ በኢትዮጵያ ትልቅ ፋብሪካ አለው፤ 70 በመቶ ያህሉ ምርቶቹ ወደ ተለያዩ ሀገራት ይላካሉ፡፣ በተለይ በአፍሪካ ሀገራት ላይ የራሱን ኩባንያ በመክፈት ምርቶቹ እንዲሸጡ እያደረገ ይገኛል፡፡ በዚህም ድርጅቱ ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር ችሏል፡፡

ምርቶቹ ጥራታቸውን የጠበቁና በሀገር ውስጥ ከሚገኙ ተፈጥሯዊ ነገሮች ተሰርተው ቀርበዋል፡፡ በሀገር ውስጥ ነው የተመረቱት ሲባል የሀገር ውስጥ ምርት ጥራት የሌለውና ዋጋውም ቢሆን ዝቅተኛ እንደሆነ ተደርጎ ይታሰብ ይሆናል የምትለው ብራንድ አምባሳደሯ፤ መወደድ የነበረበት የሀገር ውስጥ ምርት መሆኑን ገልጻለች፡፡ «ለራሳችን ቆዳና የጸጉር ዓይነት ተስማሚ እንዲሆን ተደርጎ ከተሰራ እኛ መምረጥ ያለብን ይህን ምርት ነው፡፡ እስካሁን ደንበኞቻችን ምርቶቹን ወደውታል፤ ያልሞከሩትም ሞክረው አይተው መውደድ ብቻ ሳይሆን በሀገራቸውም ምርት ሊኮሩ ይገባል» በማለት ምክረ ሀሳቧን ለግሳለች፡፡

# ትዝብት/ ማረፊያ

## መንገዶች ያስ ዕቅድ ነው የሚፈርሱት?

**ዋስልኝ አየለ**

ባለፈው ዓርብ ጠዋት ኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በር ላይ ከሚገኙ ጫማ ከሚያጸዱ ልጆች ከአንደኛው ጋ ጫማዬን ለማስጠረግ ልቀመጥ ስል መንገድ የሚያጸዱ ሴቶች አካባቢውን በአቧራ ጉም አስመሰሉት፡፡ እያጨሱት ጫማ የሚያጸዱት ልጆች ጋ ደረሱ፡፡ ልጆቹ ተነስተው አቧራው ወደማይጨስበት ቦታ ራቅ አሉ፡፡ እኔም ተከትዬ አብሬያቸው ቆምኩ፡፡

ይሄኔ አንደኛው ልጅ እየተናደደ «በጠዋት አያጸዱም እንዴ!፤ በጠዋት እኮ ነው ማለቅ ያለበት» ሲል ሌላኛው ደግሞ «አቧራ እኮ ነው ግን ምኑን ይጠርጉታል? በእጅ የሚነሳውን ብቻ አንስተው ለምን አይሄዱም? ይሄ እርሻ የሆነ መንገድ ምኑ ይጠረጋል?» ሲል ብሶቱንም ግርምቱንም ገለጸ፡፡

ልጁ እንደዚያ ሲል ነው እኔም ልብ ብዬ ማስተዋል የጀመርኩት፡፡ የሚጠረገው መንገድ የተቆፋፈረ አቧራ ነው። የተቆፈረ መሬት ላይ ያለ አቧራ ደግሞ ተጠርጎ አያልቅም፡፡ የሚጠረገው አስፋልት ሲሆን ነው፡፡ አስፋልት ከሥር አቧራ ስለማያወጣ ከላይ ያለውን ሲጠርጉት ይጸዳል፡፡ የተቆፋፈረ መንገድ ግን መሬቱን የቱንም ያህል ቢጠርጉት አፈር ከሥር እየወጣ ይሄዳል። ሲጠረግም እየጨሰ ሌሎች አካባቢዎችን ጭምር ይበክላል እንጂ አይጸዳም፡፡ እንዲያውም አቧራ የሌለውን አስፋልት እንደገና አቧራ መጨመር ነው፡፡

ይህ ሁሉ የሆነው ግን በጽዳት ሠራተኞች ችግር አይደለም፡፡ የእነርሱ ችግር ምናልባትም ከጠዋት 1፡00 በፊት ጨርሱ ተብለው በራሳቸው ድክመት መንገደኛ እስከሚበዛ አስረፍደውት ከሆነ ነው፡፡ መንገደኛ ሲበዛ ለእነርሱም ለመጥረግ ያስቸግራል፡፡ ከዚያ ውጭ ግን ችግሩ መንገዱን ያፈረሰው አካል ነው፡፡ ይህ ችግር በተደጋጋሚ ቢጮህበትም አሁንም ችግሩ ሊቀረፍ አልቻለም፡፡

የእግረኛ መንገዶች የሚፈርሱበት የራሱ ምክንያት ይኖረዋል፡፡ ያንን ምክንያት ግን አብዛኛው ነዋሪ አያውቅም። ነዋሪው የሚያውቀው ለጥገና የሚፈርስ መንገድ ሊሰራ እንደሚችል ነው፡፡ አፍርሶ የሚተውበትን ምክንያት የሚያውቀው አፍራሹ (ሰሪው) አካል ብቻ ነው፡፡ በመሃል ግን መንገደኛ ይጉላላል፤ የከተማዋ ውበትም ይበላሻል፡፡ ዝናብ ሲዘንብ ጭቃ፣ ፀሐይ ሲወጣ አቧራ ይሆናል፡፡ በዝናብ ወቅት የመንገድ ጠርዝ ላይ በመንጠልጠል ሰርከስ የምንሰራ መስለን ነው የምንሄደው፡፡ እንዲህ የበጋ ወቅት ሲመጣ ደግሞ አቧራው አካባቢውን የእርሻ ማሳ ነው የሚያስመስለው፡፡

ቀደም ሲል እንዳልኩት አንድ መንገድ ሲፈርስ የራሱ ምክንያት ይኖረዋል፡፡ የተሻለ አድርጎ ለመሥራት (ለማደስ)፣ ወይም ሌሎች የሚጨመሩ ነገሮች ሲኖሩ ማፍረስ ያለ ነው። ዳሩ ግን መንገዱን ማፍረስ ሲጀመር የሚጠናቀቅበት ጊዜ አብሮ አይታቀድም ወይ? አንዳንድ መንገዶች በአንድ ጀንበር ፈርሰው እናገኛቸዋለን፤ ለመሥራት ግን በጋ እና ክረምት ሲፈራረቅባቸው እናያለን። እግረኛና ተሽከርካሪ ይደባለቅባቸዋል፡፡ ተሽከርካሪዎች ተደርድረው መሃል ከተማ ላይ የደረቅ ወደብ ማራገፊያ ይመስላል፡፡

በዚሁ እግረ መንገድ አንድ ትዝብት ልጨምር። አንዳንድ የእግረኛ መንገዶች ለዕድሳት ተብለው እንደገና ይሰራሉ፡፡ ለምሳሌ ኮንክሪት የነበረው ቴራዞን ይደረጋል። የሚነጠፈው ቴራዞን በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚነቃነቅ ይሆናል፡፡ ዝናብ ሲዘንብ በውስጡ ውሃ ይይዛል፤ ከዚያም ከአንደኛው ጫፍ ላይ ሲረግጡት ከዚያኛው ጫፍ ወደላይ ይነሳል፤ ከውስጡ ያለው ውሃ ልብሳችን ላይ ይረጫል ማለት ነው፡፡

ከምንም በላይ ግን አስቸጋሪ የሚሆኑት ተቆፋፍረው የሚረሱ መንገዶች ናቸው፡፡ ብዙ ጊዜ የመንገድ መቆፋፈር ቅሬታ የሚነሳው የክረምት መግቢያ ላይ ነው፤ አቧራ እንደ ችግር አይታይም፡፡ ከጭቃ በላይ ግን አደገኛ የሚሆነው አቧራ ነው፡፡ ጭቃ በዓይን የሚታይ ስለሆነ እንጸየፈው ይሆናል፡፡ አቧራ ግን በዓይን የማይታዩ ባዕድ ነገሮች አሉበት፤ ለበሽታ ይዳርጋል ማለት ነው፡፡ ምንም እንኳን አቧራ መሆኑ ችግር የለውም ተብሎ ነው ያልተሰራው ባይባልም ትኩረት ሊሰጠው ግን ይገባል፡፡

በነገራችን ላይ እነዚህን የተቆፋፈሩ መንገዶች ቶሎ መላ እንዲደረግላቸው አሳሰብኩ እንጂ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ አዲስ አበባ ውስጥ በእግር መሄድ የሚመረጥባቸው ብዙ ለዓይን ማራኪ የሆኑ የእግረኛ መንገዶችን እያየን ነው። ለምሳሌ፤ ከአራት ኪሎ ወደ ካዛንቺስ በታክሲ ከሄድኩ ይቆጨኛል፡፡ ብዙ ጊዜ አስቸኳይ ጉዳይ (ሥራ) ካልሆነ በስተቀር ካዛንቺስ የምሄደው በእግሬ ነው። ምክንያቱም ከወዳጅነት ፓርክ አንስቶ እስከ ሳይንስ ሙዚዬም ድረስ ያለው የእግረኛ መንገድ አውሮፓ ውስጥ በተንቀሳቃሽ ምስል የምናያቸውን የሰለጠኑ ከተሞች ነው የሚመስል፡፡ ይህ መንገድ ከዓመታት በፊት የቆርቆሮ አጥር እየታከክን፣ ከተቃራኒ አቅጣጫ የሚመጣ ሰው ቆመን እያሳለፍን፣ የተከማቹ የውሃ ኩሬዎችን እየዘለልን የምናልፍበት ነበር፡፡

ሌላው በዚሁ እግረ መንገድ ማንሳት የምፈልገው ደግሞ በብዙ ቦታዎች ላይ የተሰሩ የመንገደኛ ማረፊያዎች ናቸው፡፡ ከቅርቤ ልጀምርና የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በር ላይ ግራና ቀኝ ማረፊያዎች አሉ። ከአጠገቡ ደግሞ ታሪካዊ ክስተቶችን የያዙ ጋዜጦች ፎቶዎች አሉ፡፡ ብዙ መንገደኞች ሥራዬ ብለው ከዋናው መንገድ ገንጠል ብለው ገብተው ያዩታል፡፡ አንዳንዶቹ በከፍተኛ ተመስጦ አንድ በአንድ እየዞሩ ያዩታል፡፡ አሻግረው ደግሞ ከተቋሙ ሕንጻ ላይ ያሉትን የኢትዮጵያ መሪዎች ያያሉ፡፡ ይህን በሌላ ቀን እመለስበታለሁ፡፡

ይህ የመንገደኞች ማረፊያ ለብዙዎች እረፍት ማድረጊያ ነው፡፡ መመሰጫ ነው፣ መጠባበቂያ ነው። እንዲህ አይነት የመንገደኞች ማረፊያዎች በተቋማት አካባቢዎች ሊሰሩ ይገባል፡፡

በአውቶብስ ማቆሚያዎች ላይ የመንገደኞች መጠበቂያ ማረፊያዎች ተሰርተዋል፤ ችግሩ ግን መሰልጠን ገና ብዙ ስለሚቀረን አብዛኞቹ ተነቃቅለዋል። የሚሰጡትን ጥቅም በማየት ጥበቃ ልናደርግላቸው ይገባል፡፡ ከአውቶብስ መጠበቂያዎች በተጨማሪ ደግሞ በብዙ አካባቢዎች ለመንገደኞች ማረፊያ የተዘጋጁ አግዳሚ ወንበሮች አሉ። እነዚህ የመንገደኞች ማረፊያዎች የተሰሩት ጥሩ የእግረኛ መንገድ ባሉባቸው አካባቢዎች ነው፡፡

እንግዲህ እነዚህ የመንገደኞች ማረፊያዎችና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተሰሩ የሚያማምሩ የእግረኛ መንገዶች የፈጠሩት ስሜት ይመስላል በአንዳንድ የተቆፋፈሩ መንገዶች እንድንማረር አድርጎናል፡፡ አንዳንዱ ሲያሳምር አንዳንዱ ማበላሸት የተለመደ ነው።

የመንገዶች ተቆፋፍሮ መቅረት ላይ አንድ የማይገባኝ ነገር አለ፡፡ ነገሮች እንደታሰበው እንደማይሄዱ ይታወቃል። ይጠናቀቃል በተባለበት ጊዜም ላይጠናቀቅ ይችላል፡፡ ዳሩ ግን የሚጀመርበት ጊዜ (አስቻይ ሁኔታ) ሳይታወቅ ለምን ማፍረስ ላይ ይቸኮላል? ሥራው የሚጀመርበት ጊዜ ሲታወቅ ማፍረስ አይሻልም? ምክንያቱም አንድ የተቆፋፈረ መንገድ ምንም ነገር ሲሰራበት ሳናይ ለረጅም ጊዜ ይቆያል፡፡ ታዳጊ ሀገር ነንና ሁሉም ነገር ይፋጠን ለማለት ሁኔታዎች አይፈቅዱም። ዳሩ ግን ቢያንስ በተለመደው እንኳን እንድንቆይ የሚሰራበት ሁኔታ እስከሚመቻች የማፍረሱ ነገር ባይጣደፍ ይሻላል!

# ዓለም አቀፍ



## ፖሊስ አራት ባሎችን ድል ባለ ሠርግ ያገባችውን ሴት አሰረ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ፖሊስ አራት ባሎችን ድል ባለ ሠርግ ያገባችውን ሴት አሰረ፡፡ የ35 ዓመቷ ቻይናዊት ባለትዳር እና የአንድ ሴት ልጅ እናትም ነበረች። ይህች እንስት ከሰሞኑ በሀገሪቱ ፖሊስ ተይዛ መታሰሯን ተከትሎ በመላው ቻይና መነጋገሪያ ሆናለች።

ይህች ሴት በፖሊስ እንድትያዝ እና ለእስር የዳረጋት ነገር ተጨማሪ ሦስት ሰዎችን ድል ባለ ሠርግ አግብታለች በሚል ነው።ትዳር እያላት ተጨማሪ ሦስት ሰዎችን ድል ባለ ሠርግ በአደባባይ ያከበረችው ይህች እንስት ድርጊቱን ለምን አደረግሽ ተብላ ስትጠየቅ ባሌ ሁሌ በሥራ ምክንያት አብሮኝ የለም ስትል ምላሽ ሰጥታለች።

ባለቤቴ በቢዝነስ ሥራ ምክንያት ሁሌ አብሮኝ አይኖርም ይህን ያደረኩት ብቸኝነቴን ለማስወገድ ነውም ብላለች። ጥሩ ገቢ እያላቸው እና መልካም የትዳር ሕይወት እያላት ለምን ተጨማሪ ሦስት ባሎችን አገባች በሚል በመላው ቻይና ጉዳዩ አነጋጋሪ ሆኗል።

ይህች ስሟ ያልተጠቀሰችው እንስት ተክለሰውነቷ ውብ መሆኑ ወንዶቹ ብዙ ሳያጠኑ እና በፍጥነት እንዲያገቧት እንዳደረጋቸውም ተገልጿል።

እንስቷ አራቱንም ባሎቿን ፕሮግራም በማውጣት ታገኛቸው ነበር የተባለ ሲሆን ቀድሞ የነበራት ጋብቻ እንዳይታወቅባትን ሌሎች ጋብቻዎቿን ከማዘጋጃ ቤት ውጪ ባሉ ሥርዓት እንዲፈጸም አድርጋለችም ተብሏል።

በሠርጎቿ ዕለትም ቤተሰብ እና ጓደኛ መስለው የሚተውኑ ሰዎችን አዘጋጅታለች የተባለችው ይህች እንስት በመጨረሻም ለእስር ተዳርጋለች ሲል ኦዲቲ ሴንትራል ዘግቧል።

እንስቷ ለአንዱ ባሏ መንትያዎችን እንዳረገዘች እና መውለድ የምትፈልገው ወደ እናቷ ቤት በመሄድ መሆኑን መናገሯን ተከትሎ ጥርጣሬ ይፈጠራል።

የሕክምና እና ሌሎች ወጪዎችን እንዲሸፍን የተጠየቀው አንዱ ባል መጠራጠር ይጀምራል።

ይህች እንስት ሌላኛው ባሏ ጋር ሆና ሀሰተኛ የሕክምና ክትትል ማስረጃዎችን እና የተወለዱ ሕፃናትን ፎቶዎች ስትልክ ነበርም ተብሏል።

ይህ ግለሰብም በመጨረሻ ባደረገው ማጣራት ሚስቴ ነች ያላት እንስት የሌሎች ሰዎችም መሆኗን ሲያውቅ ጉዳዩን ወደ ፖሊስ ጣቢያ እንደወሰደው ተገልጿል።

አራቱም ባሎች በድምሩ የ100 ሺህ ዶላር ኪሳራ ደርሶባቸዋል የተባለ ሲሆን ብዙ ለማትረፍ የጀመረቻቸው ማታለሎች በመጨረሻም ለእስር ዳርጓታል።

## አውስትራሊያዊቷ የቀድሞ ባለቤቷን ለመግደል በመሞከርና ቤተሰቦቹን በመግደል ወንጀል ተከሰሰች

በጋዜጣው ሪፖርተር




የ49 ዓመቷ አውስትራሊያዊት ኤሪን ፓተርሰን የቀድሞ ባለቤቷን አራት ጊዜ ለመግደል በመሞከሯ ተከሰሰች። በተጨማሪ የቀድሞ ባለቤቷ ቤተሰቦች የሆኑ ሦስት ሰዎችን መርዛ በመግደል መከሰሷን ቢቢሲ ዘግቧል።

በአውስትራሊያ ቪክቶሪያ ግዛት ውስጥ በሚገኝ ቤቷ ምሳ ከጋበዘች በኋላ እንጉዳይ በመጠቀም መመረዟ ተገልጿል።

የቀድሞ ባለቤቷ ሳይመን ፓተርሰን ለመግደል እ.አ.አ. ከ2021 እስከ 2022 ባሉት ዓመታት ሦስት ጊዜ እንደሞከረች ተጠቁሟል።

አራተኛውን የግድያ ሙከራ የፈጸመችው ለቀድሞ ባለቤቷ እናትና አባት እንዲሁም አክስት ምሳ ያዘጋጀች ቀን እንደሆነና በዕለቱ ግን ባለቤቷ እንዳልተገኘ ተገልጿል።

ተከሳሿ ምግቡን ያዘጋጀችው ከወራት በፊት ከእስያውያን መደብር በገዛችው እንጉዳይ እንደሆነ ተናግራለች።

የቀድሞ ባለቤቷ እናትና አባት ምግቡን ከተመገቡ በኋላ በጠና ታመው ሆስፒታል እያሉ ሕይወታቸው አልፏል።

ተጠርጣሪዋ እንዲሁም ሁለት ልጆቿ ምንም ሕመም ስላልገጠማቸው ፖሊስ በጥርጣሬ በቁጥጥር ሥር አውሏታል።

ተከሳሿ ድርጊቱን እንዳልፈጸመች ተከራክራለች። በዋስ ለመለቀቅ ግን ጥያቄ አላቀረበችም።

ተጠርጣሪዋ እንግዶቿን የመመረዝ ዓላማ እንዳልነበራትና እሷም ምግቡን ከበላች በኋላ ታማ ሆስፒታል ተወስዳ መድኃኒት እንደተሰጣት ተናግራለች።

«እንጉዳዮቹ የምወዳቸው ሰዎች እንዲታመሙ በማድረጋቸው አዝኛለሁ» ስትል ቃሏን ሰጥታለች።

ፖሊስ ቤቷን ሲፈትሽ ያገኘውን ቁሳቁስ እስከሚመረምር ለዐቃቤ ሕግ ጊዜ እንደሚሰጥ ፍርድ ቤቱ ገልጿል።

የግድያ መርማሪው ኢንስፔክተር ዲን ቶማስ «እንዲህ የመገናኛ ብዙኃን እና የሕዝብ ትኩረት የሳበ ጉዳይ አልገጠመኝም። እዚህ ቪክቶሪያ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም አነጋጋሪ ሆኗል» ብለዋል።

በአውስትራሊያ ከፍተኛ ትኩረትን የሳበውን የክስ ሂደት ለመከታተል በርካታ መገናኛ ብዙኃን በፍርድ ቤት ተሰባስበው ነበር።

### አማራ ክልል

ይግባኝ ባይ ፡- እባባው እሸቴ መልስ ሰጪ -- በአቶ ገዛኸኝ ገ/ህይወት መካከል ስላለው የአፈፃፀም ክርክር ጉዳይ መልስ እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን አውቀው መልስዎን በጽሑፍ ይዘው ለህዳር 18/2016 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ አብክመ ጠ/ፍ/ቤት ጎንደር ምድብ ችሎት ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ ውሣኔ የሚሰጥ መሆኑን እንዲያውቁት የአብክመ ጠ/ፍ/ቤት ጎንደር ምድብ ችሎት አዟል፡፡

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

### ኦሮሚያ ክልል

ከሳሽ የምዕራብ ሐረጌ ዞን አቃቤ ህግ እና ተከሳሾች እነ ሱልጣን ሙሳ አደም 14 ሰዎች መካከል ያለውን የግድያ ሙከራ ወንጀል አስመልክቶ የምዕራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዘንድ እየታየ ያለው ፍርድ ቤት በቀን 29/10/2015 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ 2ኛ ተከሳሾች አቶ ነጆ ጀማል አልይ፣ 4ኛ አቶ አደም ሻም አብዱሌ 7ኛ አቶ ከድር አብዱላ፣ 8ኛ አቶ አብራሂም ያሲን ሸቦ፣ 11ኛ አቶ ሐሰን አብዶሽ ሙሐመድ፣ 12ኛ ጀማል ሙሳ አደም፣ 14ኛ አቶ ዩዬ አህመድ ጢቃ የሚባሉት በወንጀል የሚፈለጉ ስለሆነ ቀርበው ካልተከራከሩ ይህ ክስ በሌሉበት የሚታይ መሆኑን አውቀው በ28/2/2016 ዓ.ም 8፡30 ሰዓት እንዲያቀርቡ የምዕራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ት አዟል::

**በምዕ/ሐረ/ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

የባለንብረቱ ስም ፉአድ ነስረዲን ሰሌዳ ቁጥር 03-54865 ኦሮ የሞተር ቁጥር ፡2L-4644230 የሻንሲው ቁጥር፡ JT121LK2200021410 የሆነ ከላይ የተጠቀሰው ባለንብረት ተሸከርካሪ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር/ሊብሬ/ ጠፋብኝ ብለው በ21/02/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ስለዚህ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር/ሊብሬ/ እና ታርጋ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይገኛል ይገዛለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር/ሊብሬ/ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በኦሮሚያ ትራንስፖርት ኤጀንሲ የቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ጽ/ቤት**

የባለንብረቱ ስም ጥላሁን ገላን ተሸከርካሪው አይነት ሚኒባስ ሰሌዳ ቁጥር 3-42947 ኦሮ የሻንሲው ቁጥር፡ LH113-0179895 የሞተር ቁጥር ፡ 3L-4536717 ከላይ የተጠቀሰው ተሸከርካሪ /ሊብሬ/ ጠፋብኝ ብለው በ 19/2/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሊብሬ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሊብሬ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በሸገር ከተማ አስተዳደር የቡራዩ ክፍለ ከተማ ትራንስፖርት ኤጀንሲ**

### አዲስ አበባ አስተዳደር

አመልካች ወ/ሮ ሸዋረግ ዘውዴ እና ተጠሪ ሌተናል ኮረኔል ፍቃዱ ዱባለ በአድራሻቸው ተፈልገው ሊገኙ ስልቻሉ ለ10/3/2016 ዓ.ም በ3፡45 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ 11ኛ ቤተሰብ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

አመልካች አቶ ዘርኡ ሀብተአብ እና ተጠሪ ወ/ሮ ፀጋ ስዩም መካከል ባለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በቀን 07/03/16 ዓ.ም በ5፡00 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ 4ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ በቀጠሮ ቀን ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንዲሰጥ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

የባለንብረቱ ስም ናኦል አበራ የተሽከርካሪ ዓይነት ባጃጅ የሠሌዳ ቁጥር 01-83216 ኦ/ሮ የሻንሲ ቁጥር MD/16628 የሞተር ቁጥር የሊብሬ ቁጥር 0229808 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በቀን 13/2/2016 ዓ.ም አመልክቷል።
ይህንን ሰሌዳ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በሸገር ከተማ አስተዳደር የገፈርሳ ጉጄ ክፍለ ከተማ ትራንስፖርት ጽ/ቤት**

በከሳሽ/አመልካች /ፍ/ባለመብት፡- 1ኛ ኢትዮጵያ መድን ድርጅት
በተከሳሽ/ተጠሪ/ባለዕዳ፡- 1ኛ መላኩ ወራሹ ረታ
መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 4ኛ ባ/ኢ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በፅሁፍ ለ04/03/2016 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡ እና ክስ ለመስማት 05/3/2016 ዓ.ም በ3፡40 ሰዓት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሣሽ ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ እና በተከሣሽ ዶክተር በዳሳ መኮንን መካከል ስላለው የፍታብሔር ክስ ጉዳይ በተመለከተ ተከሣሽ መከሰሶዎን አውቀው በሬጅስትራር ክፍል ቀርበው የተሻሻለውን ክስ በመውሰድ መልሳቸውን በፅሁፍ አዘጋጅተው ለህዳር 17 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እንዲያቀርቡ ክስ ለመስማት ለህዳር 20 ቀን 2016 ዓ.ም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ድ/ዳ 1ኛ ፍታብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

ከሳሽ/አመልካች፡- መ/አለቃ ተመስገን ገለታ
ተከሳሽ/ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሙሉቀን ብርሃን ወንድማገኝ
መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 4ኛ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ ተጠሪ በ06/3/2016ዓ.ም በ4፡25 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**


በከሳሽ/ሾች ህምሳ አለቃ በላቸው በቀለ ጋምቤሮ እና ተከሳሽ ወ/ሮ ትርሐስ ገብረስላሴ ተስፋዬ መካከል ስላለው የባልና ሚስት ክስ ጉዳይ ተከሳሽ በ3/03/2016ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ በ3፡30 ሰዓት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የካ ምድብ 1ኛ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

የባለንብረት ስም አብይ ንጋቱ ጥሩነህ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-00536 የተሽከርካሪዉ አይነት የመስክ ተሽከርካሪ የሻሲ ቁጥር RC115-100004 ሞዴል RC/15 የሞተር ቁጥር MI3A-1102397 የሊብሬ ቁጥር 449961/460028
ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 21/2/2016 አመልክተዋል፡፡
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# ስፖርት



## ፌዴራል ፖሊስና ኦሮሚያ ፖሊስ የ10ኛው የጎዳና ላይ ውድድር አሸናፊ ሆኑ

ዓለማየሁ ግዛው

10ኛው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የ30 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ የሩጫ ውድድር በትናንትናው ዕለት በቢሾፍቱ ከተማ ሲካሄድ፣ ፌዴራል ፖሊስና ኦሮሚያ ፖሊስ አጠቃላይ አሸናፊዎች ሆነዋል። ከፍተኛ ፉክክር ባስተናገደው ውድድር በወንዶች ፌዴራል ፖሊስና በሴቶች ኦሮሚያ ፖሊስ የቡድን አሸናፊና የዋንጫ ተሸላሚ መሆን ችለዋል።

12 አትሌቶችን ያሰለፈው ፌዴራል ፖሊስ በወንዶች 31 ነጥቦችን በመሰብሰብ የዋንጫ ተሸላሚ ሲሆን በሴቶች ሁለተኛ ደረጃን በመያዝ ፈጽሟል። ኢትዮ ኤሌክትሪክና ኦሮሚያ ክልል በ35 እና 44 ነጥቦች ሁለተኛና ሦስተኛ ደረጃን በመያዝ የብርና የነሐስ ሜዳለያ ተሸላሚ መሆን ችለዋል። 24 አትሌቶችን ያሰለፈው ኦሮሚያ ፖሊስ በበኩሉ በሴቶች 21 ነጥቦችን ሰብስቦ የውድድሩ አጠቃላይ አሸናፊ በመሆን የዋንጫና የወርቅ ሜዳለያ ተሸላሚ በመሆን አጠናቋል፡፡ ፌዴራል ፖሊስ በ61 እና መቻል በ65 ነጥቦች 2ኛ እና 3ኛ ደረጃን በመያዝ ውድድራቸውን ፈፅመዋል።

በወንዶች መካከል በተካሄደው ውድድር ከፍተኛ ፉክክር የታየ ሲሆን፣ አንዷለም በላይ ከፌዴራል ፖሊስ ባለ ድል ሊሆን ችሏል። አትሌቱ በ1:31'33" ሰዓት ውድድሩን ያተናቀቀ ሲሆን፣ ቀዳሚ ለመሆን ከመቻል፣ ከኢትዮ ኤሌክትሪክና ከንግድ ባንክ አትሌቶች ብርቱ ፉክክር ገጥሞት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ከ25 ኪሎ ሜትር ጀምሮ ከተፎካካሪዎቹ ተነጥሎ ፍጥነቱን በመጨመር የወርቅ ሜዳሊያውን አጥልቋል። 2ኛ ሆኖ ያጠናቀቀው ሰቦቃ ንጉሴ ከኦሮሚያ ክልል በ1:32'11 ሰዓት በመግባት የብር ሜዳለያ ተሸላሚ ሲሆን ክብሮም ደስታ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በ1:32'15" ሰዓት 3ኛ ደረጃን በመያዝ የነሐስ ሜዳሊያውን ወስዷል።



በወንዶች ፌዴራል ፖሊስና በሴቶች ኦሮሚያ ፖሊስ የቡድን አሸናፊና የዋንጫ ተሸላሚ መሆን ችለዋል፣

ከውድድሩ መጀመሪያ አንስቶ ከፍተኛ ፉክክር ባስተናገደው የሴቶች ውድድር ፍቅርተ ወረታው ከመቻል ቀዳሚ ሆና ማጠናቀቅ ችላለች፡፡ ባለ ድሏ አትሌት ከ20 ኪሎ ሜትር በኋላ ብቻዋን በመሮጥ 10 ኪሎ ሜትሩን በድንቅ ብቃት ጨርሳለች። በዚህም ከተፎካካሪዎቿ በ400 ሜትር ርቀት ቀዳሚና የውድድሩ አሸናፊ በመሆን የወርቅ ሜዳለያ ተሸላሚ ሆናለች፡ ፡ አትሌቷ የ30 ኪሎ ሜትሩን ውድድር ለመጨረስ 1:45'30 የሆነ ሰዓት አስፈልጓታል፡፡ ጋዲሴ ሙሉ ከኦሮሚያ ፖሊስ በ1:46"27 ርቀቱን በማጠናቀቅ 2ኛ ሆና የብር ሜዳሊያውን አጥልቃለች፡፡ የኔነሽ ጥላሁን ከኦሮሚያ ክልል በ1:46'28 ሰዓት በመግባት 3ኛ ሆና ውድድሯን በመጨረስ የነሐስ ሜዳለያ ባለቤት ሆናለች።

በወንዶች ፉክክሩን በበላይነት የፈፀመው የፌዴራል ፖሊሱ አትሌት አንዷለም በላይ በውድድሩ ያስተናገደው ፉክክር ከባድ እንደሆነና በቡድን ሥራ ጥሩ ውጤት እንደተመዘገበ ተናግሯል። ሲዘጋጅ የነበረው በውጭ ሀገር ለሚካሄዱ የማራቶን ውድድሮች በመሆኑም በውድድሩ ውጤታማ እንዲሆን እገዛን እንዳደረገለት ከውድድሩ በኋላ ለአዲስ ዘመን አስተያየት ሰጥቷል፡፡ የውድድሩ ቦታም ሞቃት ከመሆኑ በቀር እሱና የቡድን ጓደኞቹ ዝግጅታቸውን ካደረጉበት ስፍራ የሚቀራረብና ምቹ እንደነበረ ገልጿል። አክሎም በውድድሩ የታየው መተጋገዝና የቡድን ሥራው በሌሎች ውድድሮች ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ብሏል።

የሴቶች ውድድር አሸናፊዋ የመቻል አትሌት ፍቅርተ ወረታ በበኩሏ፣ ውድድሩ ጥሩ እንደሆነና ያደረገችው ዝግጅት ለድል እንዳበቃት ጠቁማለች። ባደረገችው ጠንካራ ዝግጅትም እንደምታሸነፍ እርግጠኛ እንደነበረች ተናግራለች። ለዚህም አሠልጣኟ በደንብ እንዳዘጋጃትና ከፍተኛውን ትንቅንቅ እንደምታሸንፍ ነግሯት ወደ ውድድሩ እንደገባች ገልፃለች፡፡

ለውድድሩ አሸናፊ አትሌቶች እንደየደረጃቸው ሽልማት የተበረከተላቸው ሲሆን፤ በሁለቱም ጾታ 1ኛ ደረጃን በመያዝ ላሸነፉ አትሌቶች 40 ሺ. ብር በሽልማት መልክ ተበርክቷል። 2ኛ ደረጃን በመያዝ ውድድራቸውን ለፈጸሙ አትሌቶች 20ሺ. ብር የተበረከተ ሲሆን 3ኛ ደረጃን በመያዝ ላጠናቀቁት አትሌቶች ደግሞ የ18 ሺ.ብር ሽልማት ተሰጥቷል። ሽልማቱ ከ4ኛ እስከ 8ኛ ደረጃን በመያዝ ላጠናቀቁ አትሌቶችም እንደየ ደረጃቸው ከ16 ሺ. እስከ 8 ሺ. ብር ሽልማት ተሰጥቷል። በተጨማሪም አንጋፋ አትሌቶችም ከስድስት ሺ. ብር ጀምሮ እስከ እስከ 5 መቶ ብር ሊበረከትላቸው ችሏል። ፌዴሬሽኑ ለሽልማት በአጠቃላይ 318 ሺ. ብር ወጪ አድርጓል።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በ2016 ዓ.ም ከሚያካሂዳቸው የውድድር ዓይነቶች አንዱና የመጀመሪያው የሆነው የ30 ኪ.ሜ የጎዳና ውድድር ኢትዮጵያን በአህጉርና ዓለም አቀፍ ውድድሮች የሚወክሉ ውጤታማና ተፎካካሪ አትሌቶችን ለማፍራት ዓላማን አንግቦ የሚካሄድ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ከዘጠኝ ክለቦች፣ አራት ክልሎች፣ አንጋፋ አትሌቶችና የግል ተወዳዳሪዎች ጠንካራ ፉክክር ማድረግ ችለዋል። 322 ወንድና 108 ሴት አትሌቶች በአጠቃላይ 430 አትሌቶችም በውድድሩ ተሳትፈዋል፡፡


# የጨረታ ማስታወቂያ

ደንበኛ፡- በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ርፖሬሽን የሀዋሳ ኢንዱስትሪያል ፓርክ ቅ/ጽ/ቤት

የጨረታዉ አይነት ለሃዋሳ ኢንዱስትሪያል ፓርክ ቅ/ጽ/ቤት የጥበቃ አገልግሎት ግዢ

የግዥ መለያ ቁጥር IPDC/HIP/NCB/NC/02/2016

በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የሀዋሳ ኢንዱስትሪያል ፓርክ ቅ/ጽ/ቤት ለጽ/ቤቱ የጥበቃ አገልግሎት በሃገራዊ ግልጽ ጨረታ የግዢ ዘዴ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡ ስለሆነም መስፈርቱን የምታሟሉ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የጨረታ ሰነዱን በመግዛት መወዳደር የምትችሉ መሆኑን እናሳውቃለን።

1. ይህ ግዢ በጀቱ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን በሀዋሳ ኢንዱስትሪያል ፓርክ ቅ/ጽ/ቤት የሚሸፈን ይሆናል፡፡
2. በጨረታው መሳተፍ የሚችሉት የታደሰ ህጋዊ ንግድ ፍቃድ ያላቸው 1 ህጋዊ የንግድ ምዝገባ ሰርተፍኬት ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉ የግብር ከፋይ መለያ /TIN/ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው።
3. የጨረታው ሰነድ በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተዘጋጀ ሲሆን የማይመለስ ብር 500 (አምስት መቶ ብር) ቀርበው በመክፈል በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የአንድ ማዕከል አገልግሎት አስተዳደርና ፋይናንስ ቢሮ አንደኛ ፎቅ የጨረታ ሰነድ መውሰድ ይችላሉ ።
4. የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የሥራ ሰዓት ከሰኞ እስከ አርብ ጠዋት ከ2፡00 እስከ 6፡00 ሰዓት ከሰዓት በኋላ ከ 7፡30 እስከ 11፡30 ቅዳሜ ከ2፡00 እስከ 6፡00 ሰዓት ነው።
5. ተጫራቾች የመወዳደሪያ ዋጋቸውንና ሰነዶቻቸውን ኮፒ በሁኔታዎች ላይ ባልተወሰነ የጨረታ ማስከበሪያ ብር 50,000.00 ( ሃምሳ ሺ ብር ) ከሲ.ፒ.ኦ ጋር በታሸገ ኤንቨሎፕ ከጥቅምት 22 እስከ ህዳር 13/2016 ዓ.ም ከቀኑ 8፡00 ድረስ በተዘጋጀው ሣጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው።
6. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ህዳር 13/ 2016 ዓ.ም ከሰዓት 8፡00 ሰዓት ላይ ተዘግቶ በእለቱ ከሰዓቱ በ8፡30 ላይ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የስብሰባ አዳራሽ 3ኛ ፎቅ ይከፈታል፡፡

ቅ/ጽ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**አድራሻ**

**በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የሀዋሳ ኢንዱስትሪያል ፓርክ ቅ/ጽ/ቤት**

**የአንድ ማዕከል ሕንፃ ፣1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 01፣ ስልክ ቁጥር 0462120631**

**በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የሀዋሳ ኢንዱስትሪያል ፓርክ ቅ/ጽ/ቤት**

# Invitation to Bids
# Bid No. OB-RS/002/2023

Relief Society of Tigray (REST) invites interested and eligible bidders to bid for the supply of Afridev Hand pump.

| S/N | Description | Unit Measure | Qty. |
|---|---|---|---|
| | Afridev Hand Pump with full accessories | Set | 248 |

- The bidding document shall be obtained from REST Liaison Office; Addis Ababa around Wolo Sefer, in front of Addis Zoo Peacock Park or Mekelle REST Head Office Room No. 613 against payment of non-refundable Birr 300.00 (Three hundred birr only).
- All bids must be accompanied by a bid bond amounting to 2% of the offer in the form of a bank guarantee or CPO.
- Bid should be submitted to REST Liaison Office or Head Office in Wax-sealed envelope before or on the closing date. The closing date will be on November 13, 2023, at 5:00 pm.
- Bid will be opened on November 14, 2023, at 3:00 pm in the presence of Bidders or their representatives who prefer to attend at REST Head Office, Mekelle-Tigray.
- REST reserves the right to accept or reject the bid.

**Relief Society of Tigray (REST)**
**P.O. Box 8078**
**Mob. +251-941-35-71-76**
**Addis Ababa**
**or**
**Relief Society of Tigray (REST)**
**P.O. Box 20**
**Tel. +251-034-440 99 96/40 63 00**
**Fax +251-034-440 67 14**
**Mekelle, Tigray**

**Relief Society of Tigray (REST)**